Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ
SEEK WISDOM, ELEVATE YOUR INTELLECT AND SERVE HUMANITY !

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒትስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ጋዜጠኝነትና፣ኮምኒዩኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሑፍ ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአማርኛ መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸው የፅሁፋዊ ግብረ መልሶች ትንተና (በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በ በየነች ፀጋዬ

መስከረም/2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# የአማርኛ መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸው የፅሁፋዊ ግብረ መልሶች ትንተና (በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒትስ፣የቋንቋዎችጥናት፣ጋዜጠኝነትና፣ኮምኒዩኬሽን ኮሌጅ

የአማሪኛ ቋንቋ ስነ-ፅሑፍ ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለ በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ በየነች ፀጋዬ

አማካሪ

ግርማ ገብሬ (ዶ/ር)

መስከረም/2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**የአማርኛ መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸው የፅሁፉዊ ግብረ መልሶች ትንተና (በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)**

**በ በየነች ፀጋዬ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| ------------------------------------ | ----------------------- |
| **አማካሪ** | **ፊርማ** |
| ------------------------------------------ | ----------------------- |
| **ፈታኝ** | **ፊርማ** |
| ------------------------------------------ | ----------------------- |
| **ፈታኝ** | **ፊርማ** |

## ምስጋና

ከሁሉም አስቀድሜ ያለ እርሱ የማይሆንና ሁሉ በእርሱ ለሆነው በጊዜዊ ለፈቀደው ልኡል እግዚአብዜር ምስጋና ይድረሰው፡፡

የጥናቴን ርዕስ አቅጣጫ ከማስያዝ ጀምሮ ጽሁፍን አንብቦ በመከታተል ስህተቶችን በመጠቆምና በማሳየት በማረምና በማስረዳት ደከመኝ ሰለቸኝ ሣይል ሙሁራዊ አስተያየት በመስጠት ጥናቴ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር ግርማ ገብሬ ምስጋናዬን ከታላቅ አክብሮት ጋር ይሁንልኝ በተጨማሪም ይህን ትምህርት እንድማር በተለየ መልኩ ችግሮቼን በመጋፈጥ ልጆቼን እያሳደ ትልቅ መስዋት ለከፈለልኝ ብርታት ለሆነኝ ለውድ ባለቤቴ ለነርስ በላይ ፈጠነ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ባለህበት ይድረሰህ ትልቅ ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ በመቀጠልም ይህ ጥናት ተጀመሮ እስኪያልቅ ድረስ ችግሬ ችግርሽ ሆኖ በርካታ ድጋፍ ላደረግሽልኝ ለውድ እናቴ መምህርት ወጋየሁ ተሾመ ምስጋናዬና ፍቅሬ በቃላት ባይገለጽም ፈጣሪ ረዥም ዕድሜና ጤና ባለሽበት እንዲሰጥልኝ ከልብ እመኝልሻለሁኝ፡፡ እንዲሁም እዚህ ደረጃ እንድደርስ ስትመኝ ለነበርከው ዛሬ ግን በህይወት የሌለኸው በጣም ለምወድህ ለውድ አባቴ ለመምህር ጸጋዬ ጉዲና እና ለእህት ወንድሞቼ በሙሉ በሃሳብ ያልተለያችሁኝ ጠቅላላ ቤተሰቦቼ ምስጋናዬ ከልብ ይሁንልኝ፡፡

በመጨረሻም ለጥናቴ አጋዥ የተለያዩ መሳሪያዎችን ድጋፍ ላደረገልኝ ስራዬ እንዲፋጠን የተለያዩ እገዛ ላደረገልኝ ለስራ አለቃ ለመምህር ደጀኔ ተንኮሉ እና ለስራ ባልደረቦቼ እንዲሁም ለጓደኞቼ ለመምህርት ጽጌ ግርማ ለመምህርት ይርጋለም መኮንን እና ለመምህርት ብርትኳን ይገረም እና ምናለ በሽር ላቅ ያለ ምስጋነዬ ባላቹበት ይሁንልኝ፡፡

# የይዘት ማዉጫ

ገጽ

ምስጋና ..... i
የሰንጠረዥ ማውጫ ..... v
አጠቃሎ ..... vi
ምዕራፍ አንድ ..... 1
መግቢያ ..... 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 2
1.3.የጥናቱ ዓላማ ..... 3
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ..... 4
1.6 ሙዳዬ ቃላት ..... 4
ምዕራፍ ሁለት ..... 5
ክለሳ ድርሳናት ..... 5
2.1. የፅሀፈት ትምህርት ፅንስ ሀሳብ ..... 5
2.1.1 የፅሀፈት ምንነት ..... 6
2.1.2. የፅሀፈት ትምህርት አስፈላጊነት ..... 7
2.1.3. የፅሀፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉት ተላውጦች ..... 7
2.2. ግብረ መልስ የሚሰጥባቸው መንገዶች ..... 8
2.2.1 የጽሑፍ ግብረ መልስ ..... 8
2.2.2 የጽሑፍ ግብረ መልስ አሰጣጥ ቅርጽ ..... 9
2.2.3. የቃላዊ ግብረ መልስ ምንነት ..... 10
2.2.4.የቃላዊ ግብረ መልስ አሰጣጥ ስልቶች ..... 11
2.2.5 የአቻ ግብረ መልስ ..... 12

2.2.6 በግል የሚከናወን ግብረ መልስ ..... 12
2.2.7 የቡድን ወይም የቢጤ ግብረ መልስ ..... 12
2.2.8 በመምህር የሚሰጥ ግብረ መልስሰ ..... 12
2.3 የግብረ መልስ ምንነት ..... 13
2.4. የግብረ መልስ ጠቀሜታ ..... 14
2.5. የግብረ መልስ አይነቶች ..... 15
2.5.1. ገምጋሚ ግብረ መልስ (Evaluative Feedback) ..... 16
2.5.2. አመቻች ግብረ መልስ (Facilitative Feedback) ..... 16
2.5.3 አስተካካይ ግብረ መልስ (corrective Feedback) ..... 16
2.5.4. ትዕዛዛዊ ግብረ መልስ (Directive feedback) ..... 17
2.6. የግብረ መልስ አሠጣጥ ስልቶች ..... 17
2.6.1. ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት ..... 18
2.6.2. ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት ..... 18
2.6.3. ጠቋሚ የአስተራረም ስልት ..... 18
2.7. የግብረ መልስ ባህርያት ..... 19
2.7.1. አሉታዊ (Negative) ባህርያት ..... 19
2.7.2. አወንታዊ (positive) ባህርያት ..... 20
2.8. የፅሁፍ ግብረ መልስ አሰጣጥ መንገዶች ..... 20
2.9. የፅሁፍ ግብረ መልስ ሚና ..... 22
2.10. ፅሁፋዊ ግብረ መልሱን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎች ..... 23
2.11. ፅሁፋዊ ግብረ መልስ የትኩረት አቅጣጫ ..... 23
2.11.1. ቅርፅን ትኩረት ያደረገ ግብረ መልስ ..... 23
2.11.2. ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ ግብረ መልስ ..... 24

2.12. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 24

ምዕራፍ ሶስት ........ 27

የአጠናኑ ዘዴ ........ 27

3.1. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ ........ 28

3.1.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 28

3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........ 28

3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 28

3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 29

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ........ 29

3.2.1 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 29

3.2.2 ቃለ መጠይቅ ........ 30

3.2.3 ምልከታ ........ 31

3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 32

ምዕራፍ አራት ........ 34

መረጃ ትንተና ........ 34

4.1. የተማሪዎች ግላዊ መረጃ ........ 34

4.1.1የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች ........ 35

4.1.2ከጽሁፍ መጠይቅ ከቃለመጠይቅ ክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 35

ምዕራፍ አምስት ........ 54

ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ ........ 54

5.1 ማጠቃለያ ........ 54

5.2. አስተያት ........ 56

ዋቢ መፃህፍት ........ 58

አባሪዎች ........ 65

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፡ የተማሪዎች ግልዊ መረጃ በተመለከተ የቀረበ ....................................................... 34

ሰንጠረዥ 2፡ የጽሁፋዊ ግብረ መልስ አይነት አሰጣጥ በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች .......... 36

ሰንጠረዥ 3፡ የመምህራን ግብረ መልስ አሠጣጥ ባህሪን በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች ..... 39

ሰንጠረዥ 4፡ የመምህራን ግብረ መልስ አሠጣጥ ስልቶችን በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች ... 41

ሰንጠረዥ 5፡ የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረ መልስ አሠጣጥ የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች ....................................................................................................... 44

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የአምርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሰጧቸውን የጽሁፍ ግብረመልሶችን መፈተሽ ነው። የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ አይነታዊ እና መጠናዊ የአጠናን ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ተጠኚዎቹም በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ከ9ኛ እስከ 11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ በማስተማር ላሉት ሁለት በምህራን እና በ9ኛ (ሀ ና ለ) በመማር ላይ ካሉት በናሙናነት የተመረጡት 45 ተማሪዎች በመረጃ ምንጭነት ተሳታፊ ሆነዋል። ተማሪዎቹ የተመረጡት በዕጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ሲሆን ለናሙና የተመረጡ መምህራን ደግሞ በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው።ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ያገለገሉ የጽሁፍ መጠይቅ ቃለመጠይቅ እና የክፍል ምልከታ ናቸው የተሰበሰቡ መረጃዎችም በአይነታዊ በመጠናዊ እና በገላጭ የመተንተኛ ስልት ተተንትነዋል። በተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ተሞልተው የተመለሱ ጥያቄዎችን ከግብረ መልስ አይነት፣ ከግብረ መልስ አሰጣጥ ባህሪ፣ ከግብረ መልስ ስልቶች ና ከግብረ መልስ የትኩረት አቅጣጫ አንጻር ተተንትነዋል። በእነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ እያንዳንዳቸው መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰት ላይ የግብረ መልስ አይነቶችን እያቀለቃሉ ቢጠቀሙም በአብላጫው ግን አስተካካይ ግብረ መልስን እንደሚጠቀሙ መረጃው ያሳያል። እነዲሁም በዋናነት ስልቶችን መርጦ የማረም ስህተቶችን መጠቀማቸውን ከምልከታውና ከመጠይቆቹ ለምረጋገጥ ተችሏል። መምህራኑ በተማሪዎቻቸው ጽሁፍ ላይ ትኩረት አድርገው ግብረ መልስ የሚሰጡት በቅርጽ ላይ መሆኑን እና የተሰጠው ምላሽ አዎንተዊ ገጽታ በአብላጫው የተላበሰ መሆኑን ከትንተናው ውጤት ለምረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን መምህራን ወደ አንዱ የሚያደላ ግብረ መልስ ከሚሰጡ ሁሉንም የግብረ መልስ ኣይነት እንደ ኣስፈላጊነታቸው እያሰባጠሩ ቢሰጡ ውጤታማ የሆነ ግብረ መልስ ማግኘትና የተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል የሚያሰድግ ይሆናል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን የማስተማር ዋና አላማው ተማሪዎች የማድመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂላቸው እንድዳብር ነው፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች የሚተላለፈውን መልዕክት አዳምጠዉና ተገንዝበዉ የመረዳት አቅማቸዉ ከፍ እንዲል፣ የተሰጣቸውን ፅሁፍ አንብበዉ ሀሳባቸውንና ፍላጎታቸውን ያለምንም ፍርሃትና እንቅፋት እንዲገልፁና በተጨማርም የነሱን የማንነት ደረጃ እንዲገልፁ የአፃፃፍ ስርዓት ተከትለዉ ሀሳባቸዉን በፅሁፍ ማስቀመጥ መቻል በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ሊዳብሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

ከቋንቋ ክሂሎት መካከል በመልዕክት ማስተላለፊየነት የሚመደቡ ክሂሎች የፅሕፈት ክሂልና የንግግር ክሂሎች ናቸው፡፡ የፅሕፈት ክሂል ከንግግር ክሂል ይልቅ እጅግ አስቸጋሪ ክሂል ነው፡፡ ለነዚህም ምክንያት የሚጠቀሱት ነጥቦች የፅሕፈት ክሂል የታላሚውን ቋንቋሰዋሰዋዊ ህግጋት፣ የዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት አመራረጥና አገባብ፣ የሀሳብ ቅደም ተከተላዊ አደራደር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና ይዘት አደረጃጀትን የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ይያያዛሉ፡፡ በተጨማሪም በክሂል ሃሰብ በምናስተላልፍበት ወቅት በንግግር ክሂል የምንጠቀምባቸውን የፊት ገፅታ፣ የድምፅ ከፍታና ዝግታ፣ የአካል እንቅስቃሴ ወዘተ የማንጠቀም በመሆኑ አስቸጋሪነቱን የጎላ የደርገዋል፡፡(Hedze 1988 እና ur 1996)ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ በሚገልፁበት ወቅት ብዙ ስህተቶችን ሲሰሩ ይታያሉ፡፡ እነዚህም ችግሮች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሊቀረፉና ሊስተካከሉ የሚችሉ ነገሮች ናቸው፡፡ አነዚህ ችግሮች ደግሞ የሚቀረፉት መምህራን ተማሪዎች በሚፅፉት ፅሁፎች ላይ ትኩረት ሰተው አስፈላጊውን የፅሁፍ እርማት ሲሰጡ ነው፡፡ ይህ የሚሰጠው እርማት ፅሁፋዊ ግብረ መልስ የሚንለው አይነት ነው፡፡

Richards (1990፣ 100)፡፡ባዬ (1987፣8) እና Nunan  (1989፣ 39) ፣ ማረው አለሙ(1987) በዚህ ሀሣብ ይስማማሉ፡፡ ግብረ መልስ የምንለው በተማሪዎችና በመምህር መካከል የሚደረግ ምልልስ(ተግባሪ) ነው፡፡ ተማሪዎች በተለያየ ደረጃ ግንዛቤያቸውን  እንዲያሠፉ፣ እንዲያጠነክሩና የተለያዩ ድርጊቶችን በማከናወን  ብቃታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም

ግብረ መልስ የተማሪዎችና የመምህራን የዕለት ተዕለት ግንኙነት ወይም በተማሪዎች እርስ በእርስ ግንኙነት ሊደረግ ይችላል፡፡

እንደ Zamel (1985) ገለፃ በመፃፍ ክሂል ትምህርት ትምህርታዊ ንድፈ ሀሳቡን በክፍል ውስጥ አተገባበሩ ላይ ከፍተኛ ክፍተት ይታያል፡፡ ይህም ሊፈጠር የቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ግብረ መልስ በሚሰጡበት ወቅት በቅርፅ ላይ በማትኮራቸው ምክንያት እንደሆነ ጨምረው ይገልፃሉ፡፡ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ይህ ለተማሪዎች የሚሠጠው ግብረ መልስ የሚያተኩረው አብዛኛዎቹ መምህራኖቹ በቅረፅ ላይ በማትኮራቸው ነው፡፡ ግብረ መልስ በተለያየ መልክ ሊቀርብ ይሚችል ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ተማሪዎች ለብጤዎቻቸው የሚያቀርቡት ግብረ መልስ (Peer feedback) ፣ ራስ ለራስ የሚቀርብ ግብረ መልስ (Self feedback) እንዲሁም በመምህራን የሚቀርብ ግብረ መልስ (teacher feedback) በመባል ይታወቃሉ (keh 1990)፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም በደብረፅጌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂልን ሲያስተምሩ በተጨማሪም ተማሪዎችን የፅሁፍ መለማመጃ በሚያፅፏቸው ወቅት በሚፅፏቸው ፅሁፎች ላይ የሚፈፅሟቸውን ማንኛውንም ስህተቶች (ችግሮች) የግብረ መልስ አሠጣጣቸው ምን እንደሚመስል መተንተን ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማጥናት ያነሳሳት አብይ ጉዳይ በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በደብረ ፅጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለረጅም አመታት በምታስተምርበት ጊዜ ያጋጠማትን ቸግሮች መነሻ በማድረግ ነዉ፡፡ይኸዉም ተማሪዎች የተለያዩ ደብዳቤዎችን፣ አንቀፅ፣የህይወት ታሪክ፣ ገጠመኞችን፣ ማመልከቻ፣ ድርሰት ወዘተ እንዲፅፉ በሚታዘዙበት ጊዜ የሚፅፉት ፅሁፍ የሰዋሰዉ ስህተት፣ የስርአተ ነጥብ ስህተት ወይንም ስርአተ ነጥቦችን በተገቢዉ ቦታ አለመጠቀም፣ የሀሳብ ተያያዥነትና ጥምረት ጉድለት፣ መደበኛና ኢ መደበኛን ቋንቋን ለይተዉ ያነመጠቀም ችግር የመሳሰሉትን ሲፈፅሙ ይታያሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ስህተቶች በተደጋጋሚ እንዳይፈፅሙና ችግሮቹ እንዲቀረፉ የመምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ መኖር ብሎም የአፈፃፀሙ ሁኔታ ተገቢ መሆን ለተማሪዎች ክሂል መዳበር አስተዋፅኦ ያለዉ መሆኑን አጥኚዋ ተረድታለች፡፡ ከዚህም በመነሳት በደብረ ፅጌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠንኛ

ክፍል የአማሪኛ ቋንቋ መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ግብረ መልስ በተገቢዉ መንገድ መሰጠት አለመሰጠታቸዉን ለማወቅ ካላት ፍላጎት የተነሳ ይህንን ጥናት ልታጠና ተነስታለች፡፡

## 1.3.የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባስ ወረዳ በደብረ ፅጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሠጧቸው ፅሁፋዊግብረ መልስ መፈተሽ የሚል አጠቃላይ አላማ ሲኖረው የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎችን ይዟል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸዉ ድርሰት ላይ ፅሁፋዊ ግብረ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ምን አይነት ግብረ መልስ እንደሚጠቀሙ መመርመር፡፡
2. ተማሪዎች ለፃፏቸዉ ድርሰቶች ግብረ መልስ ሳያገኙና ካገኙ በኃላ ያለዉን ልዩነት መፈተሽ፡፡
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚጠቀሟቸዉን የግብረ መልስ ስልቶችን መለየት፡፡
4. መምህራኑ በተማሪዎች ድርሰት ላይ የሚጠቀሙትን ግብረ መልስ አወንታዊና አሉታዊ ገፅታ መለየት፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በተማሪዎች የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ የተማሪዎችን የፅሁፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ የተማሪዎችን የፅሕፈት ክሂል ለማዳበር ወቅታዊ የግብረ መልስ አሠጣጥ ዘዴዎችን ለመምረጥና ለመተግበር ያግዛል፡፡
2. የአመርኛ ቋንቋ መምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ መስጠት የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ እንደሚያሻስል አውቀው የግብረ መልስ አሠጣጥ ችሎታቸውን ለማሣደግ ይጠቅማል፡፡
3. መምህራን ተገቢ የሆነ የግብረ መልስ አሠጣጥ ብልሃትን እንዲከተሉ ይረዳል፡፡
4. በቀጣይ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች መነሻና አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በሴሜን ሸዋ ዞን በደ/ሊባኖስ ወረዳ በደ/ፅጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ግብረ መልስ ያለውን አስተዋጽኦ መተንተን ላይ የሚያተኩር ነው። በመሆኑም ጥናቱ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሰጡትን ጽሁፋዊ ግብረ መልስ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። ሆኖም ይህ ጥናት በመምህራን ብቻ የሚሰጠውን ጽሁፋዊ ግብረ መልስ እንጂ በሌሎች አማክይነት የሚሰጡትን ግብረ መልሶች ካላት የጊዜ እጥረት በጥልቀት አይመረምርም።

## 1.6 ሙዳዬ ቃላት

- ✓ ግብረ መልስ…………በመምህር እና በተማሪ መካከል የሚደረግ ጽሁፋዊ መስተጋብር
- ✓ መ.1……………………….. ተጠያቂ መምህር ቁጥር አንድ
- ✓ መ.2 ………………………..ተጠያቂ መምህር ቁጥር ሁለት

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የፅህፈት ትምህርት ፅንስ ሀሳብ

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ፅሕፈት ነው። ከሀሳብ ማስተላለፊያነቱ አንፃር ካየነው ከንግግር ክሂል ጋርይቀራረባል። ይህ ስባል ግን በፅህፈትና በንግግር መካከል ሙሉ በሙሉ አንድናቸው ማለት አይደለም። ፅህፈት በተደጋጋሚ ሊነበብ በመቻሉ ረቂቅነት ያላቸውን ሀሳቦች በጠራ ቋንቋ ማቅረቡ፣ ከተቀባው ፈጣን መልስ ባለማስገኘቱና በመደበኛ ቋንቋ ላይ መመስረቱ ከንግግር የተለየ ያደርገዋል (Pincas 1982)። የጽህፈት ተግባሩ በንግግር ድምጾች ውክልና ባላቸውም ልክቶች አማካይነት ነው። የፅህፈት ትምህርት አስፈላጊነቱም የሚንጠቀመውን ምልክቶች በማወቅ በክሂሉ ተጠቅመን ስሜትና ፍላጎታችንን ለማስተላለፍ መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ነው። ሂደቱን በአግባቡ ለመተግበር የንግግር ድምጾችንና ወካይ የሆኑ ምልክቶችን ለይቶ በማወቅ መጠቀም ይኖርብናል።ለዚህም ነው ፅህፈትን ዕድሜ ዘመናችንን የምንማረው።

Raimes(1989)፣ Hedge እና Byrne (1988) ፅህፈት በእይታዊ ትምህርቶች ውክልና በመገልገል ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሠረቱበት ተግባቦታዊ መሣሪያ ነው። መተላለፊያ ስልቱም እይታዊ በአካላዊ ትግበራውአፋላቂ በተግባቦታዊ ባህሪውም ርቱዕ ክሂል ነው። Widdowsan; (1978)፣ Harmer (1991) ፅህፈት ተግባቦታዊ መሣሪያነቱን የተደረሰበትን ወይም የተጨበጠውን እውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሣይሆን አዲስ ሀሳብን ማፍለቂያ መንገድና ብልሃት ነው Candan and Butler (1997)። "ፅህፈት ሀሳብን በትምህርቶች ወይምበቋንቋ የሚወከል ሂደት ነው"። ሂደቱም አካልንና አእምሮን በማቀናጀት በአንድ ጊዜ በርካታ ባህርያቱን (ለምሣሌ) ይዘትን የቃላት አመራረጥና አደረጃጀትን፣ የሀሳብ አደረጃጀትን፣የአረፍተ ነገር አመሠራረትን፣ የአንቀፅ አወቃቀርን፣ ግጥምጥምነትንና ተከታታይነትን) ከግምት በማስገባት የሚከናወን ከማሰብ ጋር የተቆራኘ ውስብስብ የአእምሮ ስራ ነው Nunan (1989)፣ Pincas (1982) ጽህፈት ሲገልፁ በትምህርት አማካይነት የሚቀሰምና ደረጃዉን ጠብቆ ከሚደረግ ተከታታይ ልምድን የሚጠይቅ መሆኑን ይገልፃሉ።

### 2.1.1 የፅህፈት ምንነት

በመስኩ ልምድያላቸው ብዙ ምሁራን ስለፅህፈት ትምህርት ካላቸው አተያይ በመነሳት መፃፍ(Writing) የሚለውን ፅንስ ሀሳብ በተለያየ መንገድ ይገልፁታል፡፡ እንደ Byrne (1988፣3) አገላለፅ፣ መፃፍ ማለት የቋንቋዉን ድምፅ ምልክቶች በወረቀት ላይ ማስቀመጥ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡

ነገር ግን ፊደላትን አቀናብሮ ከማስቀመጥ ባሻገር በአእምሮ ያለውን ሀሳብ በፅሁፍ መካከል አደራጅቶ ለአንባቢው የማብራራትን ሂደት ጭምር ነው፡፡ Pincas (1982, V) መፅሃፍ ተግባቦትን ለመፍጠርና ራስን ለመግለፅ የሚያስችል ሁነኛ መሳሪያ ነው ብለው ይገልፃሉ፡፡
በአጠቃላይ ፅህፈት በቂ ዝግጅትና መማርን የሚፈልግ (በመደበኛ አውድ ውስጥ የሚቀርብ) ነው፡፡ ማንኛዉም አእምሮዉና አካሉ ጤነኛ የሆነሰው መደበኛ ባልሆነ መንገድ በአከባቢዉ የሚነገረዉን ቋንቋ በመልመድ ሊናገር ይችላል፡፡ ማለትም አንድ ሰው ለመናገርና ለመፃፍ የመለማመጃ ጤነኛ አካልን ይዞ ከተወለደ በመለማመድ መናገር ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሰው በቋንቋ እንዴት መፃፍ እንዳለበት የግድ መማር አለበት Nunan (1989, 36)፡፡

በሌላ መልኩ በድሉ (1996) የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሶ ሲገልፅ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለፅህፈት ክሂል የሚሰጡት ቦታ ከተቀሩት የቋንቋ ክሂሎች ጋር ሲነፃፀር እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ ከመፃፍ ይበልጥ ማዳመጥ፣ መናገርና ማንበብን ይፈልጋሉ፡፡ Doff, (1988) ፅህፈትን የሚፈልጉት ለትምህርታቸውና ለፈተና ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን የፅህፈት ክሂል መዳበር ለተማሪው የሚሰጠው ጥቅም ከዚህ የሰፋ ነው፡፡ ጥሩ የመፃፍ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ጥሩ የማሰብ ብልሀት እንዲያዳብሩ ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ የፅህፈት ክሂል ለተማሪው ሰፊ የሆነ ጥቅም ቢኖረውም ተማሪው ግን የሚማረው ለጠቅላላ እውቀት ሳይሆን ለውጤት ነው፡፡

ከምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛው ተማሪ ለፅህፈት ክሂል ትኩረት እንደማይሰጡና ከመፃፍ ይልቅ መዳመጥ፣ ማንበብና መናገር እንደሚፈልጉ ነው፡፡ በመሆኑም ፅህፈት ከትምህርት ክፍለ ጊዜ ውጪ ብዙ ጊዜ የማይጠቀሙበት መሆኑን ያስረዳል፡፡ ፅህፈት በባህሪው ውስብስብ ነው፡፡ በሰዋዊ ምክንያት ወይም በስብዕና ብቻ የማይገኝ የረጅም ጊዜ ልምድን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ በክህሉ ለመጠቀም በመደበኛ ቋንቋ የምንጠቀመውን የተለያ ያገላለፅ ድምፆችን የማንጠቀም መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ በትክክለኛው መንገድ ለመጠቀም የቻል ዘንድ የፅህፈት ክሂልን የማስተማር ተገቢነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

Zamel (1983)፣ Rivers (1981)፣ Biggs (1988)። የፅህፈት ክሂልን ማስተማር ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ የሚያጋጥማቸዉን ፅሁፎች ጭብጥ፣ ባህሪ፣ ቅርፅ ወዘተ መረዳት እንዲያስችላቸው ማድረግና በተግባቦት ሂደትም በተለያዩ ማህበራዊ ቦታዎች የሚደርስባቸውን ተግባራትና ተግዳሮት ራሳቸው እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ይጠቅማቸዋል። Pincas (1982) በአጠቃላይ ከምሁራን ሀሳብ የምንረዳው ፅሕፈት የሚዳብረውና ማደግ የሚችለው በተከታታይ ልምምድ በመታገዝ እየዳበረ የሚሄድ ችሎታ መሆኑንና በዚህ አኳያ የሰው ልጅ አካሉንና አእምሮውን በማቀናጀት እውቀቱን፣ ገጠመኙን፣ ሀሳቡንና ውስጣዊ ስሜቱን ለመስሎቹ የሚያስተላልፌለት መንገድ መሆኑን ነው።

## 2.1.2. የፅህፈት ትምህርት አስፈላጊነት

"የፅህፈት ክሂል ትምህርት ተማሪዎች በቃል የሚሰጣቸውን ትምህር አዳምጠውና የተለያዩ ፅሁፎችን አ ንብበው ማስታወሻ እንዲይዙና በቤት ስራና በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ፅሁፍ ነክ መልመጀዎች በፅሁፍ አቀናጅተው መግለፅ ያስችላቸዋል" Venkateswaran (1995፡104) ፅህፈትን ለማካሄድ ሃሳብንና ስሜትን ለመግለፅ የሚያስችሉት የፅህፈት ክሂል ለማዳበር መሆኑን ይገልፃሉ። (Heaton 1991፡135)ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ተማሪዎች በትምርት ቤት ውስጥ የፅህፈት ክሂል ትምህርት መማራቸው በቃል የሚሰጣቸውን ትምህርት አዳምጠው ማስታወሻ ለመያዝ ጽሁፍ ነክ መልመጃዎችን በፅሑፍ አደራጅተው ለመግለፅ እንዲችሉ የፅህፈት ክሂል ትምህርት ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳለው ያስገነዝባል።

## 2.1.3. የፅህፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉት ተላውጦች

ፅህፈትን መማርና ክሂሉን በብቃት ማዳበርን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ተላውጦች በረካታ ናቸው። ከተላውጦቹ መካከል የክሂሉ የባህሪ ውስብስብነት ፣ ይህም ሲባል አእምሮዊና አካላዊ ስራ መሆኑን፣ ለመፃፍ ብዙ ጊዜ መውሰዱን ፃሐፊውን በአንድ ጊዜ ለልዩ ልዩ ተላውጦች ትኩረት እንዲሰጥ የሚጠይቅ መሆኑና ከፍተኛ ጥረትና ድካም የሚጠይቅ ነው። ከዚህም ባሻገር ለመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ለምሳሌ፡- የተማሪው ፍላጎትና ልምድ ፣ በቂ የልምምድ ጊዜ ፣ የተማሪዎች ቁጥር የመምህሩ ስልጠና እና የማስተማር ጥበብ ፣ የማስተማር ስነ ዘዴ ምርጫና ትግበራ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅትና ምርጫ ለፅህፈት

ትምህርት መክበድና በተማሪዎች ዘንድ ለክሂሉ አለመዳበር ተፅህኖ እንደሚኖራቸው ይገመታል፡፡

Dubin & Olshtain (1986፡ 15) ማህበራዊና ስነ- ልቦናዊ ሁኔታዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚገኝ አመለካከት ከሚያሳድሩ ምክንያቶች አንዱ መሆኑን ሲገልፁ፣ ይሄዉም ከቋንቋ የሚገኝ ጥቅም ነው፡፡ በመሰረቱም ተማሪው ከቋንቋውትምህርት ጥቅም አገኝበታለው ብሎ ካሰበ ለቋንቋ አዊንታዊ አመለካከትን እንደሚያዳብር ይገለፃሉ፡፡

በተመሳሳይ Heaton (1991፡4-5) የፅህፈትን ትምህር ከባድና አስቸጋሪ የሚያደርጉትን ተውላጦች ከፃሐፊውና አንባቢ ተራክቦ ከቋንቋው ስነልቦናዊ ባህሪና ከፃሐፊ አምሮዊ ችሎታ አኳያ በሦስት ከፍለው ይገለፃሉ፡፡ እነሱም፡- ስነ-ልቦናዊ ችግር ስነ-ልሣናዊ ችግርና አምሮዊ ችግር ናቸው፡፡

## 2.2. ግብረ መልስ የሚሰጥባቸው መንገዶች

የተለያዩ ምሁራን የግብረመልስ አቀራረብን በተለያየ አቅጣጫ ሲመድቧቸው ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ፡ Arends (1997) የግብረ መልስ አሰጣጥ መንገዶችን ቃላዊ ግብረመልስ፣ ጽሑፋዊ ግብረመልስና የቪዲዮ (ቲቪ) በማለት በአይነት ይከፍሏቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ Korl (1991) ደግሞ በመምህራን የሚሰጥ ግብረ መልስ በቃል የሚከወን (oral feed back) እና በጽሑፍ የሚከወን (Written feed back) በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡

### 2.2.1 የጽሑፍ ግብረ መልስ

የጽሑፍ ግብረ መልስ መስጠት ቸል የሚባለው ጉዳይ አይደለም፡፡ መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት ግብረ መልስ ለተማሪዎች የበለጠ ግንዛቤ የሚያስጨብጣቸው (መንገድ የሚያሳያቸው) መሆን አለበት፡፡ Keh (1990፣249) እንደገለጸው ጽሑፋዊ ግብረ መልስ ማንኛውንም ግብዓት ለተጠቃሚው አካል መስጠት ማለት ነው፡፡ እንደ Hyland (2003፣2) አገላለጽ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ግብረ መልስ ተማሪው የሚፈልግበትን ነገር እንዲያገኝ ውጤታማ የሆነ የጽሑፍ ግብረ መልስ አሰጣጥን የሚመለከት ነው፡፡

### 2.2.2 የጽሑፍ ግብረ መልስ አሰጣጥ ቅርጽ

Ramies (1983) እንደገለጸው በጽሑፍ የሚሰጥ ግብረ መልስ የቀረበውን ሀሳብ አሳጥሮ የመጻፍ ቅርጽን ይከተላል፡፡ የተለያዩ ጥያቄ በመጠየቅ፣የተለያዩ ሀሳብን በመስጠት ተግባራዊ የሚያደርግ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Ferhis እና ሌሎች (1997) እንደገለጹት ለተማሪዎች ጽሑፋዊ ግብረ መልስ አሰጣጥ አራት አይነት ቅርጾች አሉት፡፡ እነሱም፡- በጥያቄ መልክ፣ በትዕዛዛዊ መልክ፣ በገለጻ እና በአጋኖአዊ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡ እነዚህን ቅርጾች ስንመለከት የተለያዩ ተግባራትን ይዘው ይገኛሉ፡፡

1. በጥያቄ ፡- ሌላ ተጨማሪ የሆኑ መረጃን መጠየቅ፡
2. በትዕዛዛዊ ፡- የተለያዩ አቅጣጫን በመጠቆም ሀሳብ በመስጠት፡
3. በገለጻ ፡- አዳዲስ መረጃን መስጠትና ክለሳ ማድረግ፡
4. በአጋኖአዊ ፡- ተማሪው የሰራውን ስራ አወንታዊ የሆነ ግብረ መልስ በመስጠት ለምሳሌ፡ - ጥያቄ በመጠየቅ፣ ይህ ምን ማለት ነው ይህ ምሳሌ ምንድነው እነዚህ የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪው በሰራው ስራ ላይ እንደገና ተመልሶ በማየት (በመከለስ) እንዲሁም ግልጽ ያልሆነ ይዘት ማብራሪያ የጎደለውን ነገር በማየትና ትኩረት በመስጠት ያግዛል፡፡

Sanja (2016) እንደገለጸው በጽሑፍ የሚሰጥ ግብረ መልስ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙበት የግብረ መልስ አይነት ነው፡፡ ሂደቱም አስተያየት መጻፍንና እርማት መስጠትን የሚመለከት ነው፡፡ Weigle (2002) እንደገለጸው የጽሑፍ ግብረ መልስ በተማሪዎች ስራ ላይ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ይዘቱ፡- የጽሑፍ ዝግጅትን እና ሰዋሰዋዊ የቃላት አጠቃቀምን የመሳሰሉትን የሚመለከት ነው፡፡ የጽሑፍ ግብረ መልስ ዋና አላማው ጽሕፈትን ለማስተማር የሚጠቅም መመሪያ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በአጠቃላይ የግብረ መልስ አተገባበር ስልቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ግብረ መልሶችን እንደሚያዳብሩት የክሂል አይነት የሚለያዩ ሲሆን አንዳንድ ብቻ መርጠው መጠቀም የተዋጣለትና ብቸኛ መንገድ አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ስሌቶችን አዘበራርቆ መጠቀም የተማሪዎችን ፍላጎት እና ምኞት እንደሚጨምር ይታመናል፡፡ መምህራን የሚሰጡት ግብረ መልስ በአወንታዊ እና በአሉታዊ መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በአወንታዊ መልክ የሚቀርቡ ግብረመልሶች ተማሪዎችን የሚያነቃቃና የሚያበረታታ ሲሆን በአሉታዊ

መልክ የሚቀርቡ ግብረ መልሶች ደግሞ ተማሪዎችን ሊያሸማቅቅና ሊያሳቅቅ ስለሚችል ስሌታዊ በሆነ መንገድ መሰጠት አለባቸው።

**የአቻ ግብረ መልስ**

ተማሪዎች ከአቻቸው ግብረ መልስ የመቀበል ሃሳብ የመጣው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከሚማሩ ተማሪዎች ነው። ለመምህራን አስፈላጊ አማራጭ የሚሆነው ደግሞ ለሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች መሰረት በማድረግ ነው። የአቻ ግብር መልስ የጻሃፊውን የጥሩ ጽሁፍ ንድፈ ሃሳብ ለማሻሻል እና የአንባቢውን ግንዛቤ ለማሳደግ ይጠቅማል ተብሎ ይታመናል። ነገርግን መምህራን በአጠቃላይ ከተማሪው የበለጠ አዎንታዊ አስተሳሰብ በመያዝ ግብረመልስ መስጠት ያስፈልጋቸዋል። ቢሆንም የዚህ ጠቀሜታ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በተግባር ለማረጋገጥ በጣም አስቸጋሪ ነው።

**የግል ግብረ መልስ**

ጽሁፋዊ ግብረ መልስ ተማሪዎቹ ለጽሁፍ ያላቸውን ሃላፊነት ከፍ ከማድረጉ በላይ የሰዋሰዋዊ ስህተቶችን ለማሻሻል እገዛ ያረጋል። በሌላ በኩል የቡድን ወይም የቢጤ ግበረ መልስ በቡድን በመሆን በክፍል ውስጥ የሚከናወን በመሆኑ ለጽፈት ትምህርት ከፍተፋ አስተዋጾ አለው። በቡድን የሚቀርበውን ግብረ መልስ የበለጠ ተጨባጭ ለምድረግም የቋንቋ መምህራን ለተማሪዎቹ የግብረ መልሱን መስፈረቶች በተመለከተ ሊያሳዉቋቸው ይገባል።

**በመምህራን የሚሰጥ ግብረ መልስ**

በመምህራን የሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረ መልስ ከቡድን የግብረ መልስ አሰጣጥ በተሸለ መንገድ የተምሪዎቹን ስድሰት ለማረም የሚመረጥ አለመሆኑን አስመልክቶ የተለያዩ አከራካሪ ነጥቦች አንዳሉ ይገልጻሉ።

## 2.2.3. የቃላዊ ግብረ መልስ ምንነት

ይህ ቃላዊ ግብረ መልስ በይዘት አደረጃጀትና በቋንቋ አጠቃቀም ስልቶች ላይ የሚያተኩር ነው። ይህ ስልት ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት እና እርስ በእርስ በመሆን ለተወሰነ የጊዜ ቆይታ ተግባራዊ የሚደረግ የማስተማሪያ ዘዴ ነው Hyland (2003)። ይህ ቃላዊ ግብረ መልስ በስህተት ወይም በድክመት ላይ ትኩረት በማድረግ የይዘቱን አደረጃጀትና የቋንቋ

አጠቃቀም ግንባር ለግንባር በመገናኘት ለተወሰኑ ደቂቃዎች ብቻ በአንድ ተማሪ ጽሑፍ ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ ይህ በቃል የሚሰጥ ግብረ መልስ የሚያተኩረው ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በመጠይቅ፣ በትዕዛዝ፣ በማድነቅና አስተያየት በመስጠት ይቀርባል፡፡ እነዚህ የቃላዊ ግብረ መልስ አሰጣጥ ዘዴዎችን ስንጠቀም የዓረፍተ ነገሩን ትክክለኛነት፣ የዓረፍተ ነገሩን አወቃቀር፣ የሀሳብ አደረጃጀትንና የሰዋሰው ቅደም ተከተሉን በጥሩ ሁኔታ ተደራጅቶ መቅረቡን ስህተት የሰሩበትን ቦታ በማሳየት፣ ስህተታቸውን እንደገና አስተካክለው እንዲሰሩ በማድረግ፣ ስህተት የሰሩበትን ቦታ ወዲያውኑ በማሳየት እና ስህተታቸውን ግልጽ በሆነ መንገድ በመጠየቅ ስህተቱን በመድገም ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ Hyland (2006) William ን ጠቅሶ ቃላዊ ግብረ መልስ በቃል ምልልስ ይቀርባል፡፡ መምህራን ለተማሪዎች ቀጥተኛ የሆነ አስተያየት በመስጠት እርስ በእርስ በመግባባት የሚሰጡትን ቃላዊ ግብረ መልስ ማስታወሻ ይወስዳሉ፡፡

## 2.2.4.የቃላዊ ግብረ መልስ አሰጣጥ ስልቶች

ይህ ቃላዊ ግብረ መልስ በክፍል ውስጥ ሲከናወን በማንኛውም መንገድ በቃለ ምልልስ ይቀርባል፡፡ በዚህ መንገድ ሲከናወን የእያንዳንዱን የተማሪውን ቋንቋ ለማዳበርና ለማሳደግ በተቻለ መጠን ሊረዳ ይችላል፡፡ ቀደም ሲል በ1974 Sinclair and Cauthrd እንዳጠኑት እነዚህን የንግግር ክፍሎችን በክፍል ውስጥ በሰፊው በማቀናጀትና በማጠናከር መጠቀም ግልጽና አጭር የሆኑ ተግባራቶችን ለማከናወን ይረዳል፡፡

Sansa Hadzic (2016) እንዳየነው ገለጻ ይህ ቃላዊ ግብረ መልስ በሁለት ዓይነት መንገድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እነሱም፡- አወንታዊ ግብረ መልስ ወይም አድናቆት (positive praise) ማስቀመጥና አሉታዊ ግብረ መልስ (corrective feedback) ናቸው፡፡ ይህ አወንታዊ ወይም አድናቆታዊ ግብረ መልስ የምንለው በጣም ጥሩ ነው፣ እሽ ጥሩ ነው፣ ጥሩ፣ በርታ እየተባለ የሚሰጥ የግብረ መልስ ዓይነት እንደሆነ (Ellis 2008) ይገልጻል ፡፡ አሉታዊ ግብረ መልስ የሚባለው ደግሞ Veliz (2013) እንደሚገልጸው ይህ አይነቱ የቃላዊ ግብረ መልስ አሰጣጥ በቃል (በግልጽ) ወይም ውስጣዊ (ስሜታዊ) በሆነ መልኩ ሊሰጥ የሚችል የግብረ መልስ አይነት ነው፡፡ መምህሩ ለተማሪው ውስጣዊ (ስሜታዊ) ግብረ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪው የሰራውን ስህተት (ግድፈት) በተደጋጋሚ እራሱ ለይቶ ስህተቱን እራሱ በመረዳት እርማት መስጠት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ መምህሩ በግልጽ ወይም በቀጥታ ለተማሪው የጻፋትን ድርሰት ወይም ዓረፍተ ነገር ስህተት ነው በማለት መንገር ወይም ማሳየት ነው፡፡

## 2.2.5 የአቻ ግብረ መልስ

ተማሪዎች ከአቻቸው ግብረ መልስ የመቀበል ሃሳብ የመጣው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ከሚማሩ ተማሪዎች ነው፡፡ ለመምህራን አስፈላጊ አማራጭ የሚሆነው ደግሞ ለሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪ ተማሪዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የአቻ ግብረ መልስ የጸሃፊውን የጥሩ ጽሁፍ ንድፈ ሃሳብ ለማሻሻል እና የአንባቢውን ግንዛቤ ለማሳደግ ይጠቅማል ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገር ግን መምህራን በአጠቃላይ ከተማሪው የበለጠ አዎንታዊ አስተሳሰብ በመያዝ ግብረ መልስ መስጠት ያስፈልጋአዋል" ቢሆንም የዚህ ጠቀሜታ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በተግባር ለማረጋገጥ በጣም አስቸጋሪ ነው (Hyland,K.2003)፡፡

## 2.2.6 በግል የሚከናወን ግብረ መልስ

ይህ በግል የሚከናወን ግብረ መልስ ጽሁፋዊ ግብረ መልስ ተማሪዎቹ ለጽሁፍ ያላቸውን ሃላፊነት ከፍ ከማድረጉመ በላይ የሰዋሰዋዊ ስህተቶችን ለማሻሻል እገዛ ያደርጋል፡፡

## 2.2.7 የቡድን ወይም የቢጤ ግብረ መልስ

ይዚህ ግብረ መልስ አሰጣጥ በቡድን በመሆን በክፍል ውስጥ የሚከናወን በመሆኑ ለጽህፈት ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጾ አለው በቡድን የሚቀርበውን ግብረ መልስ የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግም የቋንቋ መምህራን ለተማሪዎቹ የግብረ መልሱን መስፈርቶች በተመለከተ ሊያሳውቋዋቸው ይገባል" (Kroll 1991:proto 2000)"

## 2.2.8 በመምህር የሚሰጥ ግብረ መልስሰ

በመምህራን የሚሰጠው ጽሁፋዊ ግብረ መልስ ከቡድን የግብረ መልስ አሰጣጥ በተሻለ መንገድ የተማሪዎቹን ድርሰት ለማረም የሚመረጥ አለመሆኑን አስመልክቶ የተለያዩ አከራካሪ ነጥቦች እንዳሉ Ur(1996) ይገልጻሉ፡፡

## 2.3 የግብረ መልስ ምንነት

ስለ ግብረ መልስ ምንነት ብዙ ምሁራን የትምህርት መስካቸውን መሰረት አድርገው የተለያዩ ሃሳቦችን ሲሰነዝሩ ተስተውለዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ Wajneryb (1992:49) ግብረ መልስ ተማሪዎች ለሰሩት ማንኛውም ክንዉን የተማሪዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ መምህሩ የሚሰጠው አፀፋዊ ምላሽ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ አክለውም ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች በኩል በፅሁፍና በንግግር የፈለቁ መልሶችን የቋንቋ መምህራን ካነበቡ እና ካዳመጡ በኋላ መልሳቸው ትክክል ወይም ስህተት ነው በማለት የሚሰጡት እርማት ግብረ መልስ እንደሚባልም አስፍረዋል፡፡

ሰዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍም ሆነ በንግግር ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡ ይህን የፅሑፍ ስራውን ያነበበና ንግግሩን ያዳመጠ ሰው ግለሰቡ ለማስተላለፍ የፈለገውን መልክዕት በብቃት ማስተላለፍ አለማስተላለፉን አስመልክተው Calle and Lorena (1994:25) "በፅሑፍ የተባለው ጉዳይ ተገቢነት የሌለው ነው፤ ግለሰቡ የተናገረው በዚህ በኩል ትክክል ሲሆን በዚህ በኩል ደግሞ ስህተት ነው፡፡" የሚሉ ሀሳቦችን የያዙ አስተያየቶች ግብረ መልስ ምንነትን የሚገልፁ ጽንሰ ሃሳቦች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

ተማሪውና መምህሩ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሀሳባቸውን በንንግግር ከሚለዋወጡበት ባሻገር በፅሁፍም ሀሳባቸውን ይለዋወጣሉ፡፡ ይኸውም መምህሩም ሆነ መማሪያ መፅሐፍ በሚያዝዘው መልመጃ አማካኝነት ተማሪው ፅህፈት እንዲለማመድ ይደረጋል፡፡ ተማረው በፅሑፍ የሰራውን ስራ መምህሩ አስተያየት ይሰጥበታል፡፡ ይህ አይነት አስተያየት የሚሰጥበት ክንውንም ፅሁፋዊ ግብረ መልስ ይባላል፡፡ ይህንንም Hyland (1990) ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚገልፁበት ጊዜ ያላቸውን ችሎታ አስመልክቶ መረጃ ለመስጠትና የሚታይባቸውን ስህተት ለመቀነስ የሚያግዝ የትምህርት ክንዋኔ አጋዥ መሳሪያ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ በሚገልፁበት ጊዜ የፅሕፈት ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለመለየትና ሀሳባቸውን በፅሁፍ ለማስተላለፍ ሲሉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመቀነስ የሚያስችል ከማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ግብረ መልስ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማከናወን የሚያመችና እንደ አንድ ማስተማሪያ ዘዴ የሚያገለግል መሳሪያ ነው ፡፡

## 2.4. የግብረ መልስ ጠቀሜታ

ግብረ መልስ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከሚከናወኑ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ግብረ መልስ አንድን የትምህርት ይዘት ለማስተማር ይቻል ዘንድ እንደ አንድ የማስተማሪያ ዘዴ የሚያገለግል አስተግባሪ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ግብረ መልስ በጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ ጊዜ የተማሪዎችን ስህተት ለቅሞ ለማመልከት የሚያስችል ሆኖ ይወሰድ ነበር፡፡ በዘመናዊ (ተግባቦታዊ) የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ግን ግብረ መልስ ስህተትን እንደ አንድ መረጃ ግብአት በመጠቀም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ግብረ መልስ በዘመናዊ የቋንቋ ማሰተማሪያ ዘዴነት የትምህርት አካል ተደርጎ እንደተወሰደም Jacoba et al. (1981) አስረግጠው ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ከምጋቤ ምላሽ የተገኘው መረጃ እንደ አንድ የትምህርት ግብዓት ያገለግላል ማለት ነው፡፡

ግብረ መልስ መምህራን የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ምን ያህል እንደተረዱት እንዲሁም ይዘውት የተነሱት አላማና ግብ ምን ያህል እንደተሳካላቸው ለመገምገም ያስችላቸው ዘንድ የሚጠቀሙበት መሳሪያቸው ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ግብረ መልስ ለመምህር ትልቅ ፋይዳ አንዳለው እና የተማሪዎች ፅሑፍ ስህተቶችን በግልፅ ለማሳየት ማስቻሉ ለመምህሩ ትልቅ እገዛ እንደሚፈጥርለት Leki (1990)፣ Kroll (1990) ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን የፅህፈት ትምህርት ዓላማውን ግብ ይመታ ዘንድ መምህራን ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነጥቦች እንዳሉ Kroll (1990) እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡፡

ተማሪዎች እንዲፅፉ የተፈለገበትን ዓላማ መለየት፣

ተማሪዎች የሚገኙበትን የፅህፈት ልምምድ ደረጃ መለየት፣

ተማሪዎች የፃፏቸውን ፅሁፎች ለማረም የምንጠቀምባቸውን መስፈርቶች በግልፅ ማዘጋጀት፣

ግብረ መልስ በማን እንደሚከናወን መለየት፣

በአጠቃላይ ግብረ መልስ በተማሪዎች ፅሑፍ ላይ የሚታዩ ስህተቶችን ለይቶ ለመመልከት፣ ማስተካከያ ለመስጠት፣ የተማሪውን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ለይቶ ለማመልከት ይረዳል፡፡

ተማሪዎች ለሚያከናውኗቸው እያንዳንዱ ክንውን ግብረ መልስ ሊሰጡ ግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የሰሩትን የክፍልም ሆነ የቤት ስራ በትክክል መስራት አለመስራታቸውን እንዲለዩ፣

ድክመት ጥንካሬያቸውን እንዲያውቁ፣ ድክመታቸውን ወደፊት ማሻሻል እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ስለሚያስችላቸው ለተማሪዎች በመማር ሂደት ውስጥ እጅግ ጠቀሜታ አለው። በተጨማሪም ግብረ መልስ የተማሪዎቸን በራስ የመተማመን ብቃት እንዲጨምርላቸው ከማስቻሉም በላይ ከአቻዎቻቸው ጋር የውድድር መንፈስ እንዲፈጥርላቸው እገዛ ያደርጋል።

ግብረ መልስ ተማሪው ከክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የሰራቸውን ስራዎች ምን ያክል በትክክል መስራት አለመስራቱን ለማሳየት፣ የጎደሉት ነገር ምን ምን እንደሆኑ ለመጠቆምና መረጃን ለመስጠት ፋይዳ እንዳለው Calle and Lorna (1994:25) ይገልጻሉ። በተጨማሪም Leki (1990) እና Kroll (19 90) ግብረ መልስ ተማሪዎች ፅሑፍቸውን በድጋሜ ለመከለስ የሚያስችል መሆኑ እና በራስ የመተማመኑን ስሜት እንዲዳብርና የመማር ፍላጎታቸው እንዲጨምር ማድረጉ ለተማሪ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ይገልፃሉ።

በአጠቃለይ ግብረ መልስ በማስተማሪያ ዘዴነቱ ማገልገሉ፣ ለተማሪም ሆነ ለመምህሩ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ይኸውም በማስተማሪያ ዘዴነቱ እንደግብአት ማገልገሉ፣ ለተማሪው የስራውን ውጤት የሚመዘንበት፣ መምህራን ያለሙት ዓላማ ምን ያህል ግብ እንደመታላቸው መረጃ ከመስጠት አንፃር ፋይዳው የጎላ ነው። ይኸውም ግብረ መልስ ጠቀሜታ የሚኖረው ትክክለኛ እና ሚዛናዊ ሲሆን፣ በፅሁፉ ላይ እንደሚታየው የችግር አይነት መጠንና መንስኤ ታሳቢ በሆነ መልኩ ሲሰጥ ነው Cruick Shank et al. (1990)። እኒሁ ምሁር አክለው እንደገለጹት የተማሪዎችን የእውቀትም ሆነ የክህሎት ደረጃ ያማከለ መሆን እንዳለበትም ያሳስባሉ።

## 2.5. የግብረ መልስ አይነቶች

የግብረ መልስ ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ የሚሰጥበት ስልት፣ እንዲሁም ምላሹን በሚመለከት የሚሠነዘሩ አመለካከቶች የተለያዩ መሆናቸውን በቀደሙት ንዑሣን ክፍሎች ለማየት ተሞክረዋል። እንዲሁም ዋናው ነጥብ መምህራን ግብረ መልስን በተለያየ መልኩ ሊሰጡ ይችላሉ። ነገር ግን እያንዳንዱ መምህር ግብረ መልስ ሲሰጡ ለብቻው ወይም እየደበላለቁ የሚጠቀሙ ሲሆን ግብረ መልስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ስላለው መምህራኑ ይህንን በመረዳት በአጠቃቀም ጊዜ አስፈላጊውን ትኩረትና ጥንቃቄ መስጠት ይገባቸዋል።ስለዚህ በዚህ ክፍል የምንመለከተው ዋና ዋናዎችን የግብረ መልስ አይነቶችን ነው። እነርሱም፡- ገምጋሚ ግብረ መልስ (Evaluative) አመቻች ግብረ መልስ (Facilitative) አስተካካይ ግብረ መልስ

(corrective) እና ትዕዛዛዊ ግብረ መልስ (Directive) በመባል ይታወቃሉ (Maxley;1889; Duker; 1983; Anker; 2000) (Angelo and Cross 1993;) ።

## 2.5.1. ገምጋሚ ግብረ መልስ (Evaluative Feedback)

ገምጋሚ ግብረ መልስ ተማሪዎች በሚፅፏቸው ፅሁፍ ላይ በመምህራን የሚሠጣቸው ውጤት በማየት የፃፉትን ፅሁፍ ጥሩ ፅሁፍ እንደሆነ ተረድተው በቀጣይ ፅሁፏቸው ቀሪውን ነጥብ በመሙላት ተነሣሽነት እንዲኖራቸውየሚያደርግ የግብረ መልስ አይነት ነው። ይህ ገምጋሚ ግብረ መልስ በአሠጣጡ ወቅት አብዛኛውን ግዜ ትኩረት አድርገው ውጤት የሚሠጠው በፅሁፍ ይዘት ላይ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜም በፅሁፍ ቅረፅ ላይም ትኩረት ያደርጋል። በዚህ ዘዴ በመጠቃም ምላሽ በሚሠጥበት ወቅት መምህራን በክፍል ውስጥ ተሣትፎ ለሚያደርጉ ወይም የእጅ ፅሁፋቸው የተሸለ ለሆነ ተማሪ አድሎ እንዳያደርጉ ተማሪውን አለማየትና አለማወቅ የሚስጥር መለያ ቁጥር በመስጠት እንድፅፉ ቢደረግ ተመራጭ ይሆናል (Porto 2000፣Anglo and crass 1993፣Daikerss 1989) ።

## 2.5.2. አመቻች ግብረ መልስ (Facilitative Feedback)

አመቻች ግብረ መልስ አብዛኛውን ግዜ ተማሪዎች በሚፅፏቸው ፅሁፍ ላይ የሚሠጥ የምላሽ አይነት ሲሆን ምላሹም የሚሠጠው ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን በማቅረብ መልክ የሚከናወን ነው። ጥያቄዎች በተወሰነ ጉዳይ ላይ የሚያተኩርና ጠቅለል ባለ ሁኔታ በማቅረብ ቢሠጥም ትኩረቱ በቋንቋው ይዘት ላይ በመሆኑ ለቋንቋው ቅረፅ ያለው ትኩረት አናሳ ነው (Moxley 1989)።

## 2.5.3 አስተካካይ ግብረ መልስ (corrective Feedback)

አስተካካይ ግብረ መልስ ተማሪዎች በሚፅፏቸው ፅሁፎችውስጥ የሚፈፅሙሟቸውን የሰዋስው ስህተቶችን (ግድፈቶችን) በመጠቀም አስተካክሎ ምለሽ የሚሰጥ ዘዴ ነው። ይህ ምጋቤ ምላሽ አብዛኛውን ጊዜ የሚያከናውነው ቀጥተኛ ምላሽን በመስጠትና በመተካት እንዲሁም በመሠረዝና በማጥፋት ትክክለኛውን ቅደም ተከተላቸውን በማስተካከል የሚሠጥ የግብረ መልስ አይነት ነው። Anglo 1993) (Zamel; 1985; Raimes; (1983);; በአጠቃላይ ተማሪዎች ለሚፅፋቸው

ፅሁፎች ላይ የሚፈፀሟቸው የስህተት አይነቶች የማስተካከያ ምላሽ ለመስጠት የሚከተሉትን መንገድ መከተል አስፈላጊ ነው፡፡

- ❖ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የገቡ የተሳሳቱ ቃላትና ሀረጋት፣አያያዣችና ስርዓተ ነጥቦች ወዘተ በተስማሚና በተገቢ ቃል፣ሀረግና ስርዓተ ነጥብ በመተካት ማስተካከል፡፡
- ❖ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የገቡት ቃላት፣ሀረጋት፣አያያዦችና ስርዓተ ነጥቦች አስፈላጊ ከሆነ በማስመር ወይም በማክበብ በመጠቀም ማጥፋት፡፡

በአጠቃላይ በፅሁፍ ውስጥ የቃላት ወይም የዐረፍተ ነገር ቅደም ተከተል ከተዛነፈ ድጋሚ በመፃፍ ወይም በምልክት በመጠቀምና የጎደለ ቃልና ሀረግ እንድሁም አያያዥና ስርዓተ ነጥቦች ካለ በመጨመር መስተካከል ናቸው (Lind mann፡ 1995) ፡፡

## 2.5.4. ትዕዛዛዊ ግብረ መልስ (Directive feedback)

ትዕዛዛዊ ግብረ መልስ ተማሪዎች በሚፅፏቸው ፅሁፎች ላይ ያለውን ወይም ወደ ፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ስህተቶች ወይም ግድፈቶች ተማሪዎች በራሣቸው መስተካከል እንደቻሉ እና እንዲያርሙ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ዘዴው ተማሪዎች ምን አይነት ስህተት እንደፈፀሙና እንዴት መታረም እንዳለበት እንዲያውቁ የሚረዳቸው ቢሆንም ተማሪዎች ብዙ ድካም ስለማይፈልጉ ተቀባይነቱ ዝቅተኛ ነው (daiker 1989)፡፡

እንደ Anker (2000) ገለፃ ተማሪዎች በትዕዛዝ መልክ የሚሠጥ ግብረ መልስ ተማሪዎቹ ዘንድ አብዛኛውን ጊዜ ተፈላጊነትና ተቀባይነት የለውም ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በሚፅፉት ፅሁፏቸው ላይ ቀጥተኛና ግልፅነት ያለውን ምለሽ ስለሚፈልጉ በመሆናቸው ነው፡፡

## 2.6. የግብረ መልስ አሠጣጥ ስልቶች

ተማሪዎች በፅሁፍ መለማመጃ ትምህርት ጊዜ የመፃፍችሎታቸው እንዲሻሻል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለተማሪዎቻቸው በክፍልና ከክፍል ውጪ እንዲፅፉና እንዲለማመዱ ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ግብረ መልስ በሚሠጥበት ወቅት ዋና ዋናዎችን መጠቀም ያሻል (Byrne; 1988፤ ur, 1996, Landen, 1982)፡፡

### 2.6.1. ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት

ይህን የአስተራረም ስልት የሚጠቀሙ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚታዩትን ስህተቶች ሁሉ ነቅሶና ለቅሞ በማውጣት ምላሽ የሚሠጥበት መንገድ ነው፡፡ ለተማሪዎች ይህ የአስተራረም ስልት ለታላሚው ቋንቋ ያላቸውን የሰዋስው ችሎታ ለማሣደግ የሚረዳ ስልት ቢሆንም በመምህሩ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሣድርና ጥንታዊ የአስተራረም ስልት በመባል ይታወቃል (Fregeau; 1999 Griwin 1991; Laland 1982)፡፡

### 2.6.2. ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት

ይህ የአስተራረም ስልት የሚከናወነው ስህተቶቹንና ችግሮቹን ብቻ ለቅሞ(ለይቶ) በማወጣት ማረም ሲሆን በመምህሩ ላይ የሚያስከትለውን የስራ ጫና ለማቃለልና በተማሪዎች ላይ የሚፈጥረውን የተስፋ መቁረጥ ስሜትን ለማስወገድ የሚሰጥ የአስተራረም ስልት ነው፡፡ ይህ የአስተራረም ስልት በሚሰጥበት ወቅት በተማሪዎች የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚታዩትን ስህተቶችን ሁሉ ሣይሆን በተመረጡትና በዋና ዋና ስህተቶች (Lalande 1982) ላይ ትኩረት በመስጠት የሚከናወን ነው፡፡

### 2.6.3. ጠቋሚ የአስተራረም ስልት

ይህ የአስተራረም ስልት በበርካታ ምሁራን ተመራጭ እንደሆነ ይነገራል፡፡ የአስተራረሙ ሂደት ለእያንዳንዱ ስህተት ወካይ የሆነ ምልክቶችን በመስጠት የሚከናወን ስልት ነው፡፡ ይህንን የአስተራረም ስልት ለመጠቀም በመጀመሪያ የትኛው ምልክት ለየትኛው ስህተት እንደሚያሣይ ለተማሪዎች በግልፅ አለማሣየቱ የራሱ የሆነ ድክመት ያለው ስልት ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ተማሪዎች በሚፅፏቸው ፅሁፍ ላይ /በድርሰታቸው/ ላይ የተቀመጠውን የስህተት ምልክት አይረዱትም ፡፡ Byren /1988፤ 126) ይህንን የአስተራረም ስልት መምህራን ከመጠቀማቸው በፊት የትኛው ምልክት ለየትኛው ስህተት እንደሆነ በቅድሚያ ግንዛቤ መስጠት አለባቸው Byren (1988; Raimes /1983; 152)፡፡

## 2.7. የግብረ መልስ ባህርያት

ግብረ መልስ የተለያዩ ነገሮችን መሠረት አድርጎ ከግንዛቤ ውስጥ በመስገባት በተለያየ መልኩ Calle and chan /1994/ ሲበይኑ ይታያሉ፡ ፡ለምሣሌ ቃላዊና ፅሁፋዊ ግብረ መልስ፣ይዘትና ቅርፃዊ ግብረ መልስ፣ አሉታዊና አወንታዊ ግብረ መልስ ወዘተ በመለት ይከፍሏቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ንዑስ ክፍል ስር ለማየት የሚሞከረው አሉታዊና አወንታዊ የግብረ መልስ በህሪያቶችን ነው፡፡

የተማሪዎችን የመማር ችሎታ ለማሣደግ የሚሰጠው ግብረ መልስ ወደ ፊት በርትተው እንዲሠሩ ተስፋ የሚሠጥና ትችት እንዳይኖርበት የሚያደርጉ የግብረ መልስ አሠጣጥ ሁኔታዎች ዋናዎቹ አሉታዊና (Negative) አወንታዊ (positive) በመባል የሚታወቁ የተማሪዎችን የማበረታታትና የማዳከም አስተዋፅኦ አላቸው (cavalcanti (1990) እና Leki (1990) ይገልፃሉ፡፡

### 2.7.1. አሉታዊ (Negative) ባህርያት

አሉታዊ ግብረ መልስ የፅሁፍ ትክክል አለመሆኑን በሚያሣይ መልኩ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ማሣየት አለበት፡፡ ካልሆነ ተማሪዎች ለሠሩት ስራ የሚሠጣቸውን አሉታዊ ግብረ መልስ ትችት መስሎ ስለሚታያቸው ጠቃሚ መረጃውን(መልዕክቱን) ሣይረዱ ይቀራሉ ፡፡ ስለዚህ መምህራን በተማሪዎቻቸው ፅሁፍ ላይ የሚሠጡት አሉታዊ ግብረ መልስ ሲሰጡ የተማሪዎቻቸውን ስሜት እንዳይጎዳ አግባብነትና ግልፅነት ያለውን ግብረ መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ ታማሪዎቹ ደካማ ጎናቸውን ተረድተው ማስተካከል ይችላሉ (Calle and chan 1994፤225 )፡፡

ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ ስንረዳው በመማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች ተገቢውን የአፃፃፍ ስርዓት በመረዳት የተሠማቸውን ስሜት ሀሣባቸውን በማቀነባበር እንዲፅፉና ድርሰት የመፃፍ ችሎታቸው እንዲሻሻል እና መምህራን ተገቢውን አወንታዊና አሉታዊ ግብረ መልስ መስጠታቸው ተማሪዎች ስህተታቸውን እንዳይደግሙ ይጠቅማቸዋል ፡፡

### 2.7.2. አወንታዊ (positive) ባህርያት

ይህ የግብረ መልስ ሁኔታ በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ለማቅረብ መሞከራቸውን በመምህሩ የሚሠጥ ጥሩ ፣በጣምጥሩ ፣ ትክክል እያለ ጥቆማ በመስጠት ተማሪዎቹ በሰሩት ስራ ላይ ስለ ጠንካራ ጎናቸው ከግንዛቤ በማስገባት መረጃ እየሰጠ የሚያገለግል ነው (Calle and Chan1994) በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ ወይም ተማሪዎች በሚፅፏቸው ድርሰት ላይ ጥሩ ነገር ከተገኘ በማድነቅና በመጥቀስ ምላሽ ሲሰጥ ለመምህሩ ስራው እንዲቀል ያደርጋል፡፡ መምህሩ ተማሪውን ከማድነቁ በፊት የሠራውን ስራ በትክክልና ተገቢ በሆነ መንገድ ማየት ይኖርበታል፡፡ ይህን ስንል ከሀሳብ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ድረስ ያለውን ማየት ለቀጣይ ስራው ጠንካራና ብርቱ ያደርገዋል፡፡

(Raimes/1983) በሌላ መልኩ ይህ አወንታዊ ግብረ መልስ ለተማሪዎች በሚሠጥበት ጊዜ ራስን ለማስወደድና ለአብዛኛው የሚሠጣቸው ግብረ መልስ ጠንካራ ጎን እና አወንታዊ ብቻ ከሆነ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ አያሣድግም፡፡ ይህ ስለ ሆነ መምህሩ ለተማሪው የሚሠጠውን ምላሽ በተገቢው መንገድ መሆን አለበት፡፡

በተጨማሪም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ እየተባለ የሚሠጠው ግብረ መልስ በቂ አይደለም፡፡ መልሶችን በተናጠል ከመስጠት ስህተቶችን ሊያስተካክሉ ከሚችሉ ግብረ መልሶች ጋር በማጣመር መስጠት ውጤታማ ያደርጋል (Byrne 1988)፡፡ በአጠቃላይ አወንታዊ ግብረ መልስ ለተማሪዎች መስጠት በተማሪዎቹ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ የመማር ፍላጎታቸውን የሚያሣድግና በአመለካከታቸው ላይ ለውጥ ስለሚያመጣ መምህሩ ይህን አውቆ ቢጠቀም ለተማሪው በመፃፍ ክሂል ላይ ያለውን ችግር ሊቀንስለት ይችላል፡፡

## 2.8. የፅሁፍ ግብረ መልስ አሰጣጥ መንገዶች

በፅህፈት ልምምድ ወቅት ግብረ መልስ መስጠት ያለውን ጥቅም በተመለከተ በርካታ የመስኩ ምሁራን ተቀራራቢ ሀሳብ ያላቸው ናቸው፡፡ ሀሳባቸው በጥቅሉ ሲታይ በመምህራን የሚሰጡ ግብረ መልስ በምን መልኩ ይሰጥ የሚለዉን የሚመልስ ነው፡፡ በዚህም በመምህራን የሚከናወን ግብረ መልስ በቃል የሚሠጥ ምላሽ (Oral feedback) ወይም በፅሁፍ የሚከናወን (Writing

feedback) በመባል ተጠቅሷዋል (Kroll,1991)፡፡ ግብረ መልሰ ለመስጠት በሚታሰብበት ጊዜ እንደ መነሻ የምንጠቀማቸው ነጥቦች አሉ፡-

- ፅሁፍን ለማረም ከመነሳት በፊት የተፃፈዉን የፅሁፍ ክፍል ማንበብ፤
- በፅሁፉ ላይ ያለዉን ጠንካራና ደካማ ጎን ተማሪዎች ጥንካሬያቸውን እንዲለዩ በማድረግ ስህተቶቻቸውን መንገር፤
- የሚሰጠው ምላሽ ግልፅና የሚታይ መሆን አለበት የሚሉት ናቸው (Raimes 1983)፡፡ የፅሁፍ ግብረ መልስ በተገቢው መንገድ ከተከናወነ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው በርካታ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ከነዚህም መካከል፡-
- በፅሁፍ ውስጥ ስህተቶችን በግልፅ ማስረዳት መቻሉ፣
- በተማሪዎቹ ላይ በራስ መተማመንን መጨመር፣
- ፅሁፋቸውን በድጋሚ ለመከለስ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል (Lekii 1983, Kroll; 1991)፡፡

በተማሪዎች የድርሰት ፅሁፍ ላይ የሚሰጥ ፅሁፋዊ ግብረ መልስ ስህተቶችን በግልፅ ማሣየት ይችል ዘንድ የተለያዩ የምላሽ ስልቶችን መከተል ያስፈልጋል፡፡ እነኚህ መንገዶች በፅሁፍ ግራና ቀኝ የሚቀርቡ ህዳጋዊ ግብረ መልስ (Mariginal feedback) እና በፅሁፍ መጨረሻ ላይ የሚቀርብ የማጠቃለያ ምላሽ (Terminal feedback) ናቸው፡፡ Grader (1989) ህዳጋዊ ግብረ መልስ በድርሰት ፅሁፍ ግራና ቀኝ የሚሰጥ ሲሆን የሚሰጡትም አስተያየት ይዘታዊ፣ ቅርፃዊ፣ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡

የሚሰጠውም ምላሽ አጭርና ግልፅ መሆን አለበት፡፡ ይህ ምላሽ በእያንዳንዱ መስመር ላይ የሚሰጡ በመሆኑ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምላሽ በቀላሉ ለይተው ለማወቅ ይረዳቸዋል፡፡ በሌላ አቅጣጫ የግብረ መልስ ስልቱ ደካማ ጎን በፅሁፍ ላይ የሚታዩትን አብይ ችግሮች የመምህራንን አጠቃላይ አስተያየት ለማሣየት አለመቻሉ ነው፡፡ እንደ Angelo (1993) ገለፃ የማጠቃለያ ግብረ መልስ (Terminal feedback) አሠጣጥ ከህዳጋዊ ግብረ መልስ አሠጣጥ በተለየ መንገድ በድርሰቱ መጨረሻ ላይ የሚሠጥ ሲሆን፣ አጠቃላይ ችግሮችን ለመፍታት የሚጠቅም አስተያየት የያዘ ነው፡፡ በዚህ ምላሽ ጊዜ የሚተኮርባቸው ነጥቦች ከፅሁፍ ርዕስ ውጪ ያሉ ጉዳዮችን አለመዘርዘር፣ በቂ መረጃ የማይሰጡ ያልተሟሉ ዐረፍተነገሮችን

አለመጠቀም፣ ጠንካርና ደካማ ጎኖችን በምክንያት ማቅረቡና ድርሰቱን ለማሻሻል የሚረዱ ግልፅ ጥያቄዎችን የማበረታታት፣ የማደፋፋርና በቀጣይ ፅሁፋቸው ለመከለስ የሚያነሣሡ ናቸው፡፡

በተቃራኒው የፅሁፍ ግብረ መልስ በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ በተደረገው ለውጥ አለመኖሩን የመጀመሪያ ቋንቋቸውን በተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት የተረጋገጠ ቢሆንም በትችትና በማበረታታት መካከል አለመመጣጠን ካለ ተማሪዎች ድርሰታቸውን የመከለስና ምላሹን የማስተካከል ፍላጎት እንዳይኖራቸው ያደርጋል (Winner; 1992; Kohen and Cavalcanti; 1990)፡፡

## 2.9. የፅሁፍ ግብረ መልስ ሚና

በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ የሚሰጥ የፅሁፍ ግብረ መልስ የራሱ የሆነ ሚናዎች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል የመተቸትና የማበረታታት፣ ለፅሁፍ ያለንን ትኩረት ለማስቀየር ሚና አላቸው (Liki 1990)፡፡ የፅሁፍ ግብረ መልስ የመተቸትና የማበረታታት ሚና እንዲኖረው የሚያደርጉ የግብረ መልስ ገፅታዎች በዋናነት አወንታዊ ምላሽና አሉታዊ ምላሽ በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ሚናዎች የተማሪዎችን የመፃፍ ስሜትን የመቀስቀስ ወይም የማቀዝቀዝ እና ተስፋ የማስቆረጥ ሚናም አላቸው (Liki; 1990)፡፡ በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ በመምህራን የሚከናወኑ አወንታዊ የፅሁፍ ግብረ መልስ ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር፡-

- ✓ በራስ መተማመንን ለመስጠት፣
- ✓ ተማሪዎችን ለማበረታታትና ለማነቃቃት ፣
- ✓ የግብረ መልሱን መረጃ ለመጠቀም፣ ለመከለስና ቀጣዩን ድርሰት ለመፃፍ መነሻ መሆን የሚሉት ናቸው (Troyka; 1990; Liki 1990)፡፡

## 2.10. ፅሁፋዊ ግብረ መልሱን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎች

በግብረ መልስ አሠጣጥ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚገልፀው የፅሁፋዊ ግብረ መልስ በማን ይሰጥ? በሚል መሠረታዊ ጥያቄ በራካታ ጥናቶች ተደርጓል። ፅሁፋዊ ግብረ መልስ በግል በብጤ እንድሁም በመምህራን ሊከናወን ይችላል። በግል የሚደረግ ግብረ መልስ ተማሪዎች ለፅሁፍ ያላቸውን ሀላፊነት ከፍ ከማድረጉም በላይ የስዋስው ስህተቶችን (Girammatical errors) ለማሻሻል ይረዳል።

በኩል የቡድን (የብጤ) ግብረ መልስ በቡድን በመሆን በክፍል ውስጥ የሚከናወን በመሆኑ የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ የቋንቋው መምህራን ለተማሪዎቹ የግብረ መልስ መስፈርቶች በተመለከተ ሊያሣውቃቸው ይገባል Porto፣ (2000) Kroll፣ (1991)።

Ur (1996) እንደገለፁት በመምህራን የሚሰጠው ግብረ መልስ ከቡድን የግብረ መልስ አሠጣጥ በተሸለ መንገድ የተማሪዎቹን ድርሰት ለማረም የሚመረጥ አለመሆኑን አስመልክቶ የተለዩ አከራካሪ ነጥቦች አንዳሉ ይገልፃሉ። በአጠቃላይ የፅሁፍ ግብረ መልስ በማን ይሰጥ? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ አስመልክቶ ቁርጥ ያለና ወጥ የሆነ መልስ ባለመገኘቱ ብቸኛው አማራጭ ሁለቱንም በማጣመር ማከናወን ነው። ሁለቱ በጥምረት ሲከናወኑ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሣደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ይሆናል (Chaudran 1984)::

## 2.11. ፅሁፋዊ ግብረ መልስ የትኩረት አቅጣጫ

አብዛኛዎቹ የቋንቋ ምሁራን በተማሪዎች የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰቷቸው የግብረ መልስ ትኩረታቸው ወጥ እና አንድ የሆነ መመዘኛ የላቸውም ። በተጨማሪም Zamel(1985) ምሁራን በግብረ መልስ አሠጣጥ ጊዜ አንድ አይነት አሠራር እንደለላቸው ይገለፃል።

### 2.11.1. ቅርፅን ትኩረት ያደረገ ግብረ መልስ

ይህ ግብረ መልስ ዋና ትኩረቱ በቋንቋው መሠረታዊ ሁኔታ በሰዋሰው ትክክለኝነት ፣በቃላት አመራረጥ ፣በባለቤት ግስ ስምምነት ፣በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም በፊደላት አጣጣልና በጠቅላለው ጥምረት ሁኔታ ላይ ነው (Hedge; 1988; Raimes; 1983; Zamel; 1985; Keh; 1990)።

## 2.11.2. ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ ግብረ መልስ

እንደ Kroll /1990/ ገለፃ ይዘት ላይ ትኩረት በሚደረግበት ጊዜ ሊተኮርባቸው የሚገባቸው ነጥቦች ፡-

-የርዕሱ አስፈላጊት፣

-የድርሰት አካላት መግቢያ መደምደሚያ ተገቢነት፣

-የሐሳብተ ጠያቂነት እና

- የዐአረፍተነገር አንድነትና ግጥምጥምነት እንዲሁም ጥምረት ወዘተ ናቸው።

## 2.12. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ለማየት የሚሞከረው በመምህራን የተሠሩ ፅሁፋዊ ግብረ መልስን አስመልክቶ የተደረጉ ጥናቶችን በቅደም ተከተል መመርመር ነው። የጥናቶቹን ርዕስ፣ የጥናቶቹን አላማ፣ የአጠናን ዘዴና የተገኘውን መፍትሔ በአጭሩ በማመልከት የቀረበ ሲሆን፣ በመጨረሻም ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት የሚያሣዩ ነጥቦች ተቀምጧል።

ትዕግስት (1998) "የበሳል ድርሰት መምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ትኩረት ፍተሻ" በሚል የቀረበ ነው። የዚህ ጥናት ዋና አላማ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚገኙ መምህራን የበሣል ድረሰት ኮርስን በሚያስተምሩበት ወቅት የፅህፈት ክሂልን ለማዳበር ስሉ የሚሠጡትን የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ከፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የፅህፈት አቅጣጫ አንፃ መፈተሽ ነው። አጥኚዋ ጥናቷን የካሄደችው በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ አመት ተማሪዎችን የበሳል ድርሰት ኮርስን(ELAM 101) በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ነው። አጥኚዋ ጥናቷ ግብ ይመታ ዘንድ የተጠቀመችባቸው የመረጃ መሠብሰብቢያ ዘዴዎች፡- ለመምህራኑ የቀረቡ ቃለ መጠይቆች፣ በመምህራኑ ታርመው የተመለሱ ድርሰቶች የምጋቤ ምላሽን አሠጣጥ አስመልክቶ የቀረቡ የተማሪዎች አስተያየቶችን በመጠቀም ነው።

አጥኚዋ በተሠበሰቡት መረጃዎች አማካኝነት የገኘችው የመፍትሔ ሀሳብ መምህራን ምጋቤ ምላሽን ሲሰጡ ከፅሁፍ ይዘት ይልቅ በቋንቋው ቅር ላይ ትኩረት ማድረጋቸውና የተለያዩ ምጋቤ ምላሽ አሠጣጥ አይነቶችን መጠቀማቸው ነው። ይህ ጥናት ከመጀመሪያው ጥናት ጋር ያለው ንኙነት መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ በሚሰጡት ፅሁፋዊ ግብ

መልስ ዙሪያ ማትኮሩ ነው፡፡ በተጨማሪም የመምህራን ፅሁፋዊ ግብረ ምልስ አሠጣጥ ትኩረትን በሚመለከት የተወሰነ ግንኙነት አላቸው፡፡ ይህ ጥናት ግን የመምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ እንዳለ ሆኖ በምን ዙሪያ ያተኩራል? የአሰጣጥስልቱስ፣አይነቱስ? ወዘተ... የሚል መፈተሽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከጥናቱ ጊዜ፣ ቦታ፣ ከመምህራን ደረጃ፣ ከጥናቱ ዘመን፣ ከተጠኚዎች … ወዘተ ይለያያል፡፡

እተለማሁ (2006) "የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው ይፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጡ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ፈተሸ" የሚል ነው፡፡ የጥናቱ አላማም የቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸውን ይፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ መፈተሽ ነው፡፡ አጥኚዋ ጥናቷን የደረገችው በአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የካቲት 23 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና አመራረጥ ተካሄዷል፡፡ የተጠቀመችው የመረጃ መሰብሠቢ ዘዴ፡- የፅሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና የተማ ሪነዎችን ፅሁፎች ናቸው፡፡ ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት ደግሞ አብዛኛው መምህራን አዘወትረው የሚጠቀሙት ገምጋሚ ግብረ መልስ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም በዋናነ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልትን ቢጠቀሙም ስህተቶችን ሁሉ በማረም መጠቀማቸውንም የትንተናው ውጤት አሳይቷል፡፡

እንዳለ (1992) የጥናቱ ርዕስ "በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሚና" በሚል የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማም በተማሪዎ ድርሰት ላይ መምህራን የሚሠጡት ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ የሚያመጣውን ለውጥ መመርመር ነው፡፡ አጥኚው ጥናቱን የደረገው በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በምክንያታዊ የናሙና አመራረጥ ስልት በመምረጥ ነው፡፡ በዚህ የናሙና አመራረጥ ስልት ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችን በእጣ ናሙና አመራረጥ በመጠቀም በሁለት ቡድን ከፍሎ የሙከራ ቡድንና የጥብቅ ቡድን ብሎ በመለየት የድርሰት መፃፍ ልምምድ አድርጓል፡፡ አጥኚው ለጥናቱ ግብ መምቻ የተጠቀመባቸው መረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያዎች የድርሰት ፈተናዎች፣ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ አማካይነት አጥኚው የደረሰበት ድምዳሜ ወይም የተገኘው ውጤት በቡድንና በግል ከሚከናወኑት ምላሾች ይልቅ በመምህራን የሚሰጥ ግብረ

መልስ የተሻለ መሆኑን አረጋግጧል። በተጨማሪም ፅሁፋዊ ግብረ መልስ በተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ችሎታ እንደሚሻሻል አረጋግጧል።

ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ግንኙነት ሁለቱም ጥናት ለተማሪዎች ድርሰት ትምህርት ላይ የሚሠጥ የመምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ ላይ የሚያተኩሩ  መሆናቸው ነው። ስለዚህ የቀደመው ጥናት የመምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ በተማሪዎች ላይ የሚያመጣውን ለውጥ የሚመረምር ስሆን ይህ ጥናት ግን መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸው ግብረ መልስ ትንተና መሠረት የደረገ በመሆኑ እጅጉን ይለያያሉ።

እጅጋይሁ (2011) የዚህ ጥናት ርዕስ "በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ያለው አስተዋፅኦ ትንተና" በሚል የቀረበ ነው። የጥናቱ ዋና አላማም ተማሪዎች ለሚፅፏቸው ድርሰቶች መምህራን የሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የመፃፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ መፈተሽ ነው። አጥኚዋ ጥናቷን የደረገችው በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ምድር

ወረዳ በመማር ላይ የሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በተራ የእጣ ናሙና ዘዴ ነው። የተጠቀመችው የመረጃ መሰብሰብያ መሣሪያዎች፡- በድርሰት ፈተና፣ በፅሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ አማካይነት ናቸው። ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት መምህራን የሚሰጡት ፅሁፋዊ ግብረ መልስ መመዘኛ ነጥቦች በይዘት፣ በአደረጃጀት፣ በቋንቋ አጠቃቀም፣በቃላትና በቅርፅ ችግሮች ላይ ትኩረት ቢሠጡም ተማሪዎች ንቁ ምላሽ ሰተው ቶሎ ችግራቸውን የሚቀርፉት ውርፅ ላይ መሆኑን የሚያመለክት ውጤት ተመዝግቧል።

ከዚህ ጥናት ጋር የለው ተመሳስሎሽ መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰት ትምህርት ላይ የሚሰጥ የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ የተወሰነ ምስስሎሽአላቸው። ስለዚህ የቀደመው ጥናትየመምህራን ፅሁፋዊ ግብረ መልስ በተማሪዎቻቸው ላይ የሚያመጣውን ለውጥ መመርመር ሲሆን ይህ ጥናት ግን መምህራን ለተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸው ግብረ መልስ ትንተና መሠረት የደረገ መሆኑና ከጥናቱ ጊዜ፣ ከቦታ አንፃር፣ ከመምህራን ደረጃ እና ከተጠኚዎች አኳያ ይለያያል።

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናኑ ዘዴ

ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ ስር ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የፅሁፍ መለማመጃ ላይ yì@s½¡[W ግብረ መልሶች ትንተና በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ በደብረ ፅጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት) ላይ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጠው የአጠናን ዘዴ አይነታዊ ምርምር ዘዴ (Qualitative Reseach) በዋናነት ሲሆን እንደየአስፈላጊነቱ ደግሞ መጠናዊ (Quantitative Research) ተጠቅሜአለሁ፡፡ አቀራረቡም ገለፃዊ (Discriptive) ሲሆን በዚህ መሰረት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚፈለጉ ተጠኚዎችን በተመለከተ በናሙና አመራረጥ ስልቶች ተመርጠዋል፡፡

አይነታዊ የምርምር ዘዴ በርካት የመረጃ ዘዴዎችን ተጠቅሞ (ለምሳሌ ጥልቅ የሆነ ቃለ መጠይቅ ፡ ምልከታና የተፃፉ መረጃዎችን) የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን እና ለመተርጎም ገለፃን እና ትረካን እንዲሁም አልፎ አልፎ ቁጥርን የሚጠቀም የምርምር አይነት ነው፡፡ አይነታዊ ምርምር መዘርዘርን፡ ሰፊ ገለፃን ጥልቅ ፍተሻን፡ የተጠኚዎችን ትክክለኛ ቃል የግል አመለካከትና ልምድ እንደ መረጃ ለትንተና ይጠቀማል፡፡

በአይነታዊ ምርምር፡ መረጃ ሲተነተንና ሲተረጎም ከዝርዝር ሁኔታዎች በመነሳት በተሰበሰቡ መረጃዎች ልዩነቶችና አንድነቶች ላይ በመመስረት ወደ ማጠቃለያ የመድረስ ሂደት ይከተላል፡፡

መጠናዊ የምርምር ዘዴ ስንል ከስሙ ስያሜ እንደምንረዳው ውጤቶችን በቁጥር ወይም በስታስትቲካዊ መንገድ ይተነተናል ይገረዳል፡፡ መጠናዊ ምርምር አንድን ያነሰውን ርዕስ ለማጥናት ይሞክራል እንጂ ውጤቱን ከተለያዩአቅጣጫዎች በየት ለመተንተንና ለመተርጎም አይሞክርም፡፡ መጠናዊ ምርምር ከጅምሩ በንድፈ ሃሳብ ወይም በመላምት ላይ ተመርኩዞ የሚካሄድ ምርምር ነው፡፡ መጠናዊ ምርምር በአብዛኛው በመስኩ ባለሙያዎች የታመነባቸውን ሣይንሳዊ ምርምር ተከታታይ ደረጃዎችን ተከትሎ ይሰራል፡፡ እነኚህም የጥናት ርዕስ ችግር መምረጥ የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ማድረግ መረጃ መሰብሰብ መተንተንና መተርጎም ማጠቃለያ መስጠት ናቸው፡፡

ማጠቃለያ መስጠት ናቸው። በተጨማሪ ያለው (2001፡17) መጠናዊ ምርምር በቁጥር የሚገልጽና የሚተነተንበት የምርምር አይነት እንደሆነ ይገልጻል።

በአጠቃላይ ለዚህ ጥናት በዋናነት አይነታዊ የምርምር ዘዴን መጠቀሙና እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ መጠናዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ለጥናቱ ግብ መምታት ስለታመነበትና የአተናተን ሂደቱም በትረካና በቁጥር እንዲሁም በገለፃ መልክ በመሆኑ እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ አስተማማኝ ማድረጉ፣ በመተንተንና በመተርጎም ማጠቃለያ መስጠቱ ነው፡

## 3.1. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የደብረ ጽጌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመርጧል። ይህም ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ በዛ ትምህርት ቤት ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት እያገለገለች ስለሆነ መረጃ ለመሰብሰብ አመቺ ይሆናል ብላ በማሰቧ ነው።

### 3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው ትምህርት ቤት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ደረጃዎችን ይዞ ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ የ9ኛ ክፍል በምክንያታዊ ናሙና ዘዴ ተመርጧል። ይህም የሆነበት ምክንያት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የትምህርት አመቱ እስከሚያልቅ ድረስ በትምህርት ቤት ውስጥ ስለሚገኙ አስፈላጊ የሆነውን በቂ መረጃ ለመሰብሰብ አመቺ ስለሆነ ነው።

### 3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ ተተኳሪ በሆነው ትምህርት ቤት ውስጥ ሦስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኛሉ። ከእነዚህም ከሶስቱ መምህራን መካከል አንዷ የዚህ ጥናት አቅራቢ በመሆኗ ጥናቱ ከሚደረግባቸው መምህራን አትካተትም። ስለዚህ ከአጥኚዋ ውጪ ሁለቱ መምህራን በጠቅላይ ናሙና ዘዴ እንዲሳተፉ ለናሙናነት ተመርጧል። ይህም የሆነበት ምክንያት ሁለቱን መምህራን በማሳተፍ በቂ መረጃ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል በሚል ነው።

### 3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በትምህርት ቤት በየምድቡ ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎች ከ 42 እስከ 51 የሚደርሱ ሲሆን አጠቃላይ ብዛታቸው 270 ነው። ይህንን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የምደባ ዝርዝር ብዛት ከመዝገብ ቤት የተማሪዎች ቁጥር በመመልከት ለማወቅ ተችሏል። ከእነዚህም ተምሪዎች ውስጥ ተጠኚ መምህራን የሚያስተምሩበት ስድስት የ9ኛ ክፍል ምድቦች ይገኛሉ።

ከእነዚህ ምድቦች ውስጥ ሁለቱን ምድቦች በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም (9ሀ እና 9ለ) ሁለት ምድቦች ተመርጧል። ከተመረጡት ሁለት የ9ኛ ክፍል ምድቦች በእያንዳንዱ ምድብ 45 በአጠቃላይ 90 ያክል ተማሪዎች ይገኛሉ ከ90 ተማሪዎች መካከል ከእየምድባቸው በጎዶሎ ቁጥር የሚጠሩትን 45 ተማሪዎች እጣ ጠቅልሎ ናሙና በመጠቀም መጠይቁን ሞልተዋል።

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለጥናቱ አመቺና አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሦስት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተግባር ላይ ውለዋል። እነዚህም የጽሁፍ መጠይቅ ቃለመጠይቅ እና ምልከታ ናቸው።

### 3.2.1 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ ከተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ አንደኛው ነው። መጠይቁ የተዘጋጀውም ለተማሪዎች ነው። የመጠይቁ መሰረታዊ አላማ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ነው። መጠይቆቹ የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረ መልስ አሰጣጣቸው ስኬታማ መርህን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ናቸው። መጠይቁም 45 በሚሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተሞልቷል። በተማሪዎቹ የሚሞላውም የጥያቄዎቹ ብዛት 12 ናቸው። ከእነዚህ መካከል አንድ ጥያቄ ብቻ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነጻነት እንዲግለጹ ዕድል የሚሰጥ ክፍት ጥያቄ ሲሆን ቀሪዎቹ ግን አማራጭ መልስ ያላቸው ዝግ ጥያቄዎች ናቸው። የጥያቄዎቹ አቀራረብ ለእያንዳንዳቸው ጥያቄዎች መወስኛ አራት አማራጭ በማቅረብ ነው። እነሱም በጣም እስማማለሁ (4)፡ እስማማለሁ(3) አልስማማም(2) እና ጭራሽ አልስማማም(1) ("x") በማድረግ የሚሉ አማራጮች ናቸው። የመጠይቆቹ አራት መወስኛ አማራጮች የተደረገበት ምክንያት(wens ) እና (Straton) (1980፡150) እንዲስማሙበት

የመጠይቆቹን ጠቃሚነት በውል ካለመረዳት ወይም በመሰላቸት ወይም በግዴለሽነት የተነሳ የበርካታ ተማሪዎች ምርጫ አልወስንኩም (እርግጠኛ) አይደለሁም ወደ ሚለው አማራጭ እንዳያመዝን በመፍራት ነው" ጥያቄዎቹ የተዘጋጁት የሬቲንግ ስኬል (Rating Scale) ወይም ሊከርት (Likert Scale) መሰረት በማድረግ መላሾቹ አንድ ጥያቄ ይቀርብላቸውና በዛ ጉዳይ ያላቸውን አመለካከት ባህሪ እና እምነት ሊወክል ይችላል የሚሉትን ከተሰጣቸው አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ መልስ እንዲሰጡ የሚደረግበት መጠን አመልካች የጥያቄ አይነት ነው ያለው (2001፣164) በዚህ መልክ የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ በጥናቱ አማካሪ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ እንዲሻሻሉ አስተየት የተሰጠባቸው ጥያቄዎች ማስተካከያ ተደርጎበታል በ2015 ዓ.ም በደብረ ጽጌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ሳላያ ላሉ በናሙናነት የተመመረጡ የ9ኛ ሀ እና ለ ክፍል ተምሪዎች መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት ስለአሞላሉ እና ስለ አላማው በአጥኚዋ ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡ ከዚያም በናሙናነት ተረጡ ተማሪዎች መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ጥያቄዎቹም በአባሪነት በመጨረሻላይ ተቀምጠዋል፡፡

## 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቁ የተደረገው ለጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ነው፡፡ እነሱም ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከዛ በኋላ ለእነሱ ምቹ በሆነ ጊዜና ቦታ በትምህርት ቤት ውስጥ በመገኘት (በመቅረጽ ድምጽ በካሴት በመደገፍ መረጃን ለማግኘት የ9ኛ ክፍል የአምርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ጋር ነው፡፡ በመቅረጸ ድምጽ የተቀዳውን ምልልስ ለመረጃው አተናተን ምቹ በሆነ መንገድ በጽሁፍ ወደ ወረቀት በመመለስ መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላያ የሚሰጣቸውን የግብረ መልስ አይነቶች እንዴት እንደሚሰጡና ምን አይነት ግብረመልስ እንደሚሰጡ ተምሪዎቹን እንዴት ስለግብረ መልስ ግንዛቤ እንደሚያስጨብጡና ከግብረ መልሱ በኃላ ያላቸውን ልዩነት ለማወቅ በሚያስችል መልኩ አምስት ጥያቄዎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡ የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች በአጥኚዋ ተዘጋጅተው በአማካሪ ከተገመገሙ በኂላ ተሻሽለው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

### 3.2.3 ምልከታ

ምልከታ በሦስተኛነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች በኪፍል ውስጥ የጽሁፍ ልምምድ በሚያደርጉበት ጊዜ የድርሰት መጽሃፍ ችሎታ ለውጥ ለመመዘን የሚረዳ ነው ይህመረጃ ሲሰበሰብ በክፍል ውስጥ በተግባር በመገኘት አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳና በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጡትን ግብረ መልሶች ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለማግኘት አጥኚዋን የሚረዳ ነው፡፡

ምልከታ አጥኝው የሰዎችን፣ የነገሮችን ወይም ክስተቶችን ባህሪ በአይን እየተመለከተ የተመለከታቸውንና የተገነዘባቸውን ቁምነገሮች የሚመዘግብበት ስልት ነው ምልከታ በድብቅ ወይም በግላጭ የሚደረግ የምልከታ ዘዴ ሲሆን በግልባጭ ደግሞ ሰዎቹ ምልከታ መደረጉን እያወቁ የሚደረግ ምልከታ ነው (ያዴሳ ቶለሳ 2008፡103-104)፡፡

ምልከታ ተመራማሪው ከቃለመጠይቁና ከጽሁፍ መጠይቁ ሌላ ምልከታን በመጠቀም የምንፈልጋቸውን የመረጃ አይነቶች ሊሰበስብ ይችላል፡፡ እንደ ቃለመጠይቅ እና ጽሁፍ መጠይቅ ለመላሹ ጥያቄ ቀርቦለት መላሹ ከራሱ የሚመልስ ሣይሆን ተመራማሪው ተጠኚዎቹ እያወቁ ሆነ ሳያውቁ በሚኙበት ቦታ በመሆን የእርስ በርስ ስራዎቻቸውን እና ተራክቦዎቻቸውን አስተማማኝ እና ትክክለኛ መረጃ የሚሰበስቡበት ዘዴ ነው (ያለው እንዳወቀ 1998፡182-183)፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የተጠቀመው የምልከታ አይነት በግለጽ የሚደረገውን ምልከታ ነው፡፡

ምልከታ በማካሄድ በክፍል ውስጥ መረጃዎችን መሰብሰቢያ የመከታተያ ቅጽ [chek list) ከ (Hedge)(1988፡24-26) የጽህፈት ክሂል መርሆችንና ከ Nunar) (1989115) የክፍል ምልከታ መከታተያ ዝርዝር chek list ) ሃሳብ በውሰድ በጥናቱ አማካሪ ሙያዊ አስተያየት ተሰጥቶበት ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑ ስለታመነበት በአጥኚዋ ስራ ላይ ውሏል ለናሙናነት የተመረጠውን የትምህርት ቤቱና የተጠኚዎች መምvራን ፍቃደኝነት በመጠየቅ በጊዜ ሰሌዳቸው መሰረት የምልከታ ቅጽ በማዘጋጀትና ለረዳት ተመልካቾች ደግሞ በቪዲዮ ቀረጻ እና በፎቶግራፍ ማንሻነት እንዲተባበሩኝ በማድረግ የቅድመ ተግባር ምልከታ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም ከጽሁፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ይበልጥ ለማጠናከር ሲባል አስራ አንድ ጥያቄዎችን ይዞ ተዘግጅቷል አጥኚዋ ለምልከታ የተዘጋጀውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ ፍቃደኛ የሆኑትን መምህራን በተጠየቁ ረዳትነት መርጣለች፡፡ ምልከታው እያንዳንዱ መምህር በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ አራት

አራት ጊዜ የተካሄደ ሲሆን አጥኚዋና ረዳት ፎቶግራፍ አንሺ በአንድ ላይ በመሆን ተከናውኗል" በተጨማሪም የመከታተያ ቅጽና ፎቶ ግራፎችም በተጠኚዎች ፍቃደኝነት በመጨረሻ ላይ በአባሪነት ተቀምጧል።

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መለማመጃቸው ላይ የአምርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሰጧቸው የግብረ መልሶች ትንተና የሚል ነው በዚህም አላማ ላይ ተመስረቶ ጥናቱ ይመልሳቸዋል የተባሉ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ቀርበዋል።

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰት ላይ ጽሁፋዊ ግብረ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ ምን አይነት ግብረ መልስ እንደሚጠቀሙ መመርመር።
2. ተማሪዎች ለጻፉቸው ድረሰቶች ግብረ መልስ ሳያገኙና ካገኙ በኋላ ያለውን ልዩነት መፈተሽ።
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚጠቀሟቸውን የግብረ መልስ ስልቶችን መለየት።
4. መምህራኑ በተማሪዎች መልመጃ ላይ የሚጠቀሙትን ግብረ መልስ አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታ መለየት።

የአጠናን ዘዴ በተመለከተ አይነታዊ የምርምር ዘዴ (Qualitative Research) በዋናነት ተግባራዊ የሆነ ሲሆን እነደ አስፈላጊነቱ መጠናዊ (Quantitative Research) ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል" አቀራረቡም ገለጻ decriptive) ሲሆን በዚሁ መሰረት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የተለተያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚፈለጉ ተጠኚዎች በተመለከተ በተለያዩ የናሙና አመራረጥ ስልቶች ተመርጠዋል። በጥናቱ የሚሳተፉትን ተማሪዎች ለመምረጥ ከምድቡ ክፍሎች የሚማሩት የ9ኛ ክፍል ተምሪዎች መካከል በእጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም እንዲመርጡ የተደረገ ሲሆን መምህራን ደግሞ በጠቅላይ ናሙና (Comparehesive Sampling) እንዲካተቱ ተደረጓል የጥናቱ ምንጮች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችና መምህራን ናቸው። ለጥናቱ አመቺነና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅና ምልከታ በጥቅም ላይ ውለዋል።

መጠይቆችን ትክክል ሞልተው ከመለሱት 45 ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ከመምህራን ቃለመጠይና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በትንታኔ ውስጥ ተካተዋል፡፡ ጥናቱ የገላጭ ምርምር ስልትን በመጠቀም ውጤቱን የሚገልጽ መሆኑ ያሳያል፡፡ ትንተናው ከተማሪዎች ከጽሁፍ መጠይቅ፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅና ክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎችን እንደየተቀራራቢነታቸው በማገናኘት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# መረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የአምርኛ ቋንቋ መምህራን የሚጠቀሙትን የግብረ መልስ አሰጣጥ መፈተሽ ነው ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ተተኳሪ ከሆነው ትምህርተ ቤት አስፈላጊ የሆነው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ከፍ ሲል በምዕራፍ ሦስት ስር የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ስልቶች በዋናነት ለተምሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅና የክፍል ምልከታ በተመለከተ የተለያዩ ግብረ መልስ የተሰጠባቸው ጽሁፎች የመረጃ መሰብሰቢ መሳሪያ ሆነው አገልግሎት ላይ ውለዋል በዚህ መሰረት ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ ከመምህራን ቃለመጠይቅ እና ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንደተቀራራቢነታቸው በማግናኘት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. የተማሪዎች ግላዊ መረጃ

**ሰንጠረዥ 1፡ የተማሪዎች ግልዊ መረጃ በተመለከተ የቀረበ**

| ተ.ቁ | የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ | | ብዛት በቁጥር | % | አጠቃላይ ድምር በቁጥር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጾታ | ወንድ | 17 | 37.8 | 45 | 100 |
| | | ሴት | 28 | 62.2 | | |
| 2 | እድሜ | ከ15-20 | 42 | 93.3 | 45 | |
| | | ከ21 በላይ | 3 | 6.7 | | |
| 3 | የክፍል ደረጃ | 9ኛ | 45 | 100 | 45 | 100 |

ከመጠይቆቹ የተሰጡ ላሾችን በሰንጠረዥ የተጠኚ ተማሪ ዳራዊ መረጃ በተመለከተ 42 (93.3 %) ተማሪዎች ከ15-20 ዓመት ባለ የእድሜ ክልል የሚገኙ ሲሆን 3 (6.7%) ተማሪዎች ደግሞ ከ 21 ዓመት በላይ ናቸው ጾታን አስመልክቶ 17 (37.8%) ተማሪዎች

ወንዶች ሲሆኑ 28 (62.2%) ደግሞ ሴቶች ተማሪዎች ናቸው፡፡ እድሜን በተመለከተ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከ15-20 አመት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሚገኙ ይታመናል፡፡

### 4.1.1 የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች

በናሙና በተመረጡ የክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ የመምህራን ግልዊ መረጃ በተመለከት የቀረቡ የክፍል ምልከታና ቃለ መጠይቅ የተሰጡ ምላሾች የሚያሳይ ነው የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መረጃ በተመለከተ ሁለቱም መምህራን ከ55-65 ባሉት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ የስራ ልምዳቸውን በተመለከተ ከ33-37 ዓመት የስራ አገልግሎት ያላቸው መሆኑን፣ ጾታን አስመልክቶ ሁለቱም ወንድ መምህራን መሆናቸው ነው፡፡

የትምህርት ደረጃቸውን በተመለከተ ሁለቱም ወንድ መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ ያላችው መሆኑን ያሳያል፡፡ ሁለቱም መምህራን ከ9ኛ እሰከ 11ኛ ክፍል የሚያስተምሩ ናቸው ይሁን እንጂ ሁለቱም መምህራን የተጠኚዎቹን ክፍሎች የሚያስተምሩ መሆናቸው ለጥናቱ አመቺ ይሆናል፡፡

### 4.1.2 ከጽሁፍ መጠይቅ ከቃለመጠይቅ ክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ከመምህራን ቃለ መጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

## ሰንጠረዥ 2፡ የጽሁፋዊ ግብረ መልስ አይነት አሰጣጥ በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች

| ተ.ቁ | የቀረቡ መጠይቆች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | ጭራሽ አልስማማም | | ጭራሽ ድምር | |
| | | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ |
| 1 | መምህሩ ለምጽፈው ጽሁፍ የሚሰጡኝ ግብረ መልስ በመረዳት አስተካክላለሁ፡፡ | 11 | 24.4 | 15 | 33.3 | 10 | 22.2 | 9 | 20 | 45 | 100 |
| 2 | በጻፋኳቸው ጽሁፎች ላይ መምህሬ ምንም አይነት ግብረ መልስ ሳይሰጡኝ ሙሉ ነጥብ ያስቀምጡልኛል፡፡ | 8 | 17.8 | 12 | 26.7 | 14 | 31.1 | 11 | 24.4 | 45 | 100 |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ የጽሁፍ ግብረ መልስ በመስጠት በሃሳብ አደረጃጀትና ቅደም ተከተል ላይ ትኩረት ያደርጋሉ | 7 | 15.5 | 17 | 37.7 | 5 | 11.1 | 16 | 35.5 | 45 | 100 |
| 11 | መምህሬ የሚሰጡኝን ግብረ መልስ በጻፍኳቸው ጽሁፎች ላይ የሰራሁትን ስህተት እራሴ እንዳስተካክል ትዛዝ በመስጠት ይረዱኛል፡፡ | 3 | 6.7 | 6 | 13.3 | 18 | 40 | 5 | 11.1 | 45 | 100 |

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 2 ላይ ተማሪዎች መምህሬ ለምጽፈው ጽሁፍ የሚሰጡኝ ግብረ መልስ ቶሎ በመረዳት አስተክክላለሁ ለሚለው ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ እነዚህም ጥይቄዎች በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተቀመጠው አስተካካይ ግብረ መልስ በተራ ቁጥር 2 ላይ የተቀመጠው ገምጋሚ ግብረ መልስ በተራ ቁጥር 3 ላይ የተቀመጠው አመቻች ግብረ መልስ እና በተራ ቁጥር 11 ላይ ደግሞ ትዕዛዛዊ ግብረ መልስን ወክለው የተቀመጡ ናቸው ።

እነዚህ መልሶች በተራ ቁጥር አንድ ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሠንጠረዡ እንደምንረዳው 24.4 በጣም እስማማለሁ 33.3% እስማማለሁ፣ 22.2% አልስማማም፣ 20% ደግሞ ጭራሽ አልስማማም በማለት መልሰዋል።

በዚሁ መረጃ መሰረት በቀረበው ሃሳብ ላይ 57.7% አወንታዊ ድጋፍ ሲያገኝ 42.2% ደግሞ አሉታዊ ድጋፍ አግኝቷል። ከዚህ የተረዳሁት አብዛኛው ተማሪዎች የሚሰጣቸውን ግብረ መልስ ቶሎ በመረዳት ምላሽ መስጠታቸውን መረጃው ያሳያል።

በተራ ቁጥር 2 በጻፋኳቸው ጽሁፎች ላይ መምህሬ ምንም አይነት ግብረ መልስ ሳይሰጡኝ ሙሉ ነጥብ ይሰጡኛል። ብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ 17.8% በጣም እስማማለሁ፣ 26.7 እስማማለሁ፣ 31.1% አልስማማም እና 24.4% ጭራሽ አልስማማም በማለት መልሰወዋል። በዚህ መረጃ መሰረት ከላይ ለቀረበወ ሀሳብ ላይ 44.5% አሉታዊ ድጋፍ ሲያገኙ 55.5% አውንታዊ ድጋፍ አኂኝቷል። ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው መምህራኑ በተማሪዎች የጽሁፍ መለማማጃ ላይ ግብረ መልስ ሣይሰጡ ነጥብን ብቻ ማስቀመጣቸውን ከትንታኔው ለመረዳት ተችሏል።

በተጨማሪም ከምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት መምህራኑ ለተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚጠወሙትን ዘዴ መጠቆምን በተመለከተ ለተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የተለያዩ ግብረ መልሶችን በመስጠት መጠቀማቸው የተሞከረ ሲሆን ያን ያህል የጎላ አይደለም ። ይህ ማለት ደግሞ ለተማሪው የሚሰጠው ግብረ መልስ አጥጋቢ አይደለም ማለት ነው በተጨማሪም ሌሎች ተማሪዎች ግብረ መልስን ለመቀበሉ ብዙም ተነሳሽነት ሣይኖራቸው የትምህርት ጊዜው እንደሚያበቃ ያመለክታል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች የተለያየ ጽሁፍ በሚጽፉበት ጊዜ በራስ መተማመንን እንዳይሰጣቸው መገንዘብ ተችሏል ።

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ ትኩረት አድርገው ግብረ መልስን አለመተግበራቸው ተማሪዎቹ ለሚጽፉት ድረሰት ግብረ ምለስ አጊንተው አለመለወጣቸው መቸገራቸውን ያሳያል፡፡

ጥያቄ ተራ ቁጥር 3 ላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ የጽሁፍ ግብረ መልስ በመስጠት በሃሳብ አደረጃጀትና ቅደም ተከተል ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 15.5 በጣም እስማማለሁ፣ 37.7% እስማማለሁ 11.1% አልስማማም እና 35.5 ጭራሽ አልስማማም በማለት መልስ ሰቷል" በዚህ መረጃ ላይ 53.2% ያህሉ አወንታዊ ምላሽ ሲያገኙ፡ 46.6% የሚሆኑት ደግሞ አሉታዊ መልስ ሰተዋል፡፡ እንዲሁም በተራ ቁጥር 11 ላይ መምህሬ የሚሰጡኝን ጽሁፋዊ ግብረ መልስ በጻፍኳቸው ጹሁፎች ላይ የሰራሁትን ስተት እራሴ እንዳስተካክል ትዛዝ በመስጠት ይረዱኛል፡፡ በሚለው በተመለከተ 6.7% በጣም እስማማለሁ 13.3% እስማማለሁ፡ 40% አልስማማም እና 11.1% በጭራሽ አልስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል በዚህም መጠይቅ ላይ 20% ያህሉ ድጋፍ ሲያገኙ 51.1% ደግሞ ድጋፍ አልባ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከጽሁፋዊ ግብረ መልስ አይነቶች አንጻር ከተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ አስተካካይ ግብረ መልስ 57.7%፣ ገምጋሚ ግብረ መልስ 44.5% አመቻች ግብረ መልስ 53.2% እና ትዕዛዛዊ ግብረ መልስ 20% ያህል መልስ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ከተጠቀሱት የግብረ መልስ አይነቶች ውስጥ አስተካካይ ግብረ መልስ 57.7% የሚሆነውን ከፍተኛ መጠን በመያዙ በተማሪዎች ጽሁፎች ላይ መምህራን አብዛኛውን የሚጠቀሙት ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ በተገኘው ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከተሰጡት ምልሾች መካከል አስተካካይ ግብረ መልስ ከፍተኛውን ቦት ቢይዝም መምህራኑ የተማሪዎችን ጽሁፍ በሚያርሙበት ጊዜ ገምጋሚ አመቻች እና ትዕዛዛዊ ግብረ መልስንም በመጠኑ እንደሚተገብሩ መረጃው ሣያል አስተካካይ ግብረ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ የቃላትና የዐረፍተ ነገር ቅደም ተከተልን ከተዛነፈ በድጋሚ በመጻፍ ምልክት በምድረግ እንዲሁም አያያዥና ስርአተ ነጥቦችን ካለ በመጨመር ማስተካከል ተመራጭ ይሆናል" (lind man:(1995)፡፡

በሌላ መልኩ በአጥኚዋ ምልከታ መሰረት ሁለቱም መምህራን በተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ ላይ የሃሳብ ፍሰትና አደረጃጀት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ለሚለው በተመለከት ያገኘችው ምላሽ

የተለያዩ ርዕሶችን በሚያስተምሩበት ጊዜ በዛው ክፍል ውስጥ በራሳቸው ተነሳሽነት አንቀጽ እንዲጽፉ በማድረግ ያለው ተግባር አናሳ ነው ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ በግልም ሆነ በቡድን ለጻፍት ድርሰት ስለ ንቀጽ ስፋትና አደረጃጀት የሚሰጡት ግብረ መልስ በጥልቀት በማየት የጎደለውን አያያዥና ስርአተ ነጥቦችን በመጨመር ደሚያስተካክሉና የተለያዩ የግብረ መልስ አይነቶችን በመጠቀም የትምህርት ክፍለ ጊዘውን እንደሚተገብሩ ተስተውሏል። በተጨማሪም የተለያዩ የተማሪዎችን ደብተር በመታገላብጥበት ጊዜ በደብተራቸው ላይ ድረሰቶችን ጽፈው ግብረ መልስ የሚሰጥበት ሂደቱ ውስንነት የታየበት መሆኑን ተገንዝባለች ይህ ደግሞ ተማሪዎች በቡድን እንጂ በየግላቸው የመጻፍ ፍላጎት ወይም በራስ መተማመናቸውን እንዳይጨምር ማድረጉ በተደረገው ምልከታ መገንዘብ ተችሏል ።

**ሰንጠረዥ 3፡ የመምህራን ግብረ መልስ አሠጣጥ ባህሪን በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች**

| ተ.ቁ | የቀረቡ መጠይቆች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | አልስማማም | | ጭራሽ ድምር | |
| | | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የሰጡኝን ግብረ መልስ በቀጣይ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ ምንም አይነት ዕገዛ አላደረገልኝም | 4 | 8.9 | 3 | 6.7 | 11 | 24.1 | 24 | 60 | 45 | 100 |
| 9 | የመምህሬ ግብረ መልስ ወደፊት ለምጽፈው ጽሁፍ ፍላጎት አሳድሮብኛል | 10 | 22.2 | 31 | 68.9 | 4 | 8.9 | - | - | 45 | 100 |

በሠንጠረዥ 3 ጥያቄ 8 ላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የሰጡኝን ግብረ መልስ በቀጣይ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ ምንም አይነት እገዛ አላደረገልኝም ብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በተመለከተ ለተማሪዎች የሚጠቀሙት የግብረ መልስ አሰጣጥ አስተያየቶች አወንታዊና አሉታዊ ባህሪያት

አሰጣጣቸውን ለመረዳት ነው "ከዚህ እነንጻር በተራ ቁጥር 8 ላይ ያለው ደግሞ አሉታዊ ባህሪን ሲያሳይ በተራ ቁጥር 9 ላይ ያለው ደግሞ አዎንታዊ ባህሪን የሚያሳይ ነው፡፡

በተራ ቁጥር 8 ላይ ለቀረበው የአምርኛ ቋንቋ መምህሬ በቀጣይ ለመጽፈው ጽሁፍ ምንም አይነት እገዛ አላደረገልኝም በሚለው ላይ በጣም እስማማለሁ 8.9% እስማማለሁ 6.7% እና ኣልስማማም 24.4% ፡ ጭራሽ አልስማማም 60% በማለት ምላሽ ሠተዋል፡፡

በቁጥር 9 ላይ የመምህሬ ግብረ መልስ ወደፊት ለምጽፈው ጽሁፍ ፍላጎት አሳድሮብኛል በሚለው ላይ በጣም እስማማለሁ 22.2% ፡ እስማማለሁ 68.9% እና አልስማማም 8.9% ፡ በማለት መልሰዋል ከዚህ ከተኘው መረጃ እንደምረዳው ለተማሪዎች የሚሰጠው አስተያየት 91.1% ያህል አወንታዊ ገጽታ የሚታይባቸው አስተያየት እንደሚሰጣቸው ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ መምህራኑ የሚጠቀሙበትን አስተያየቶችን በተመለከተ ተማሪዎች ለሚረፋቸው ጽሁፎች ወደ ፊት የራስ ተነሣሽነትና ፍላጎትን የሚያሳድርባቸውን ተጽኖ የሚያሳዩት አወንታዊ 91.1% እና አሉታዊውን የሚያሳዩ ደግሞ 84.4% ያህል ናቸው ስለዚህ ካገኘነው መረጃ መረዳት የሚቻለው ምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ የሚሰጡት አስተያየት አዎንታዊ መሆኑን መረጃው ይገልጻል" አዎንታዊ ሆነ አሉታዊ ግብረ መልስ በተገቢውና ሚዛናዊነቱን በጠበቀ መልኩ ቢሰጥ የተሻለ እንደሆነ call and chair (1994፡225) ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች በአጠቃላይ ግብረ መልስ ከማግኘታቸው በፊትና በሁዋላ በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ለውጥ ያለ ይመስሉታል፡፡ ብሎ ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ ላይ ሁለቱመም መምህራን አዎን ለውጥ አለ ምክንያቱም ግብረ መልስ ከማግኘታቸው በፊት የነበራቸው ድረሰትን በመጻፍ ረገድ በጣም ዝቅተኛ ነው ነገር ግን ከግብረ መልሱ በኋላ በርካታ ግንዛቤዎችን በማግኘት የመጻፍ ችሎታቸው ቀደም ሲል ከነበራቸው የተሻለ ሆኖ ይታያል፡፡

ሰንጠረዥ 4፡ የመምህራን ግብረ መልስ አሠጣጥ ስልቶችን በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች

| ተ.ቁ | የቀረቡ መጠይቆች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | አልስማማም | | ጭራሽ ድምር | |
| | | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ የሚታዩትን ስህተቶች ብቻ መርጠው ግብረ መልስ ይሰጡኛል | 17 | 37.7 | 19 | 42.2 | 6 | 13.3 | 3 | 6.7 | 45 | 100 |
| 5 | መምህሬ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ የሚታዩትን ስህተቶች በሙሉ ያርሙኛል | - | - | 5 | 11.1 | 28 | 62.2 | 12 | 26.7 | 45 | 100 |
| 6 | መምህሬ ልረዳቸው የምችለውን ምልክቶች እርማት ይሰጣሉ | 16 | 35.5 | 14 | 31.1 | 11 | 24.4 | 4 | 8.9 | 45 | 100 |

ከላይ በሠንጠረዥ 4 እንደተብራራው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የግብረ መልስ አሰጣጣቸውን በተመለከት የትኛውን ስልት እንደተጠቀሙ ለማወቅ የቀረቡ ጥያቅዎች ናቸው በተራ ቁጥር 4 ላይ ያለው በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት በተራ ቁጥር 5 ላይ ያለው ሁሉንም ስተቶች የማረም ስልት እና በተራ ቁጥር 6 ላይ ያለው ደግሞ ጠቋሚ የኣስተራረም ስልቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው፡፡

በተራ ቁጥር 4 ላይ የተበራራው ሃሳብ የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ የሚታዩትን ስህተቶች ብቻ መርጠው ግብረ መልስ ይሰጣሉ ለሚለው በተመለከተ በጣም እስማማለሁ 37.7% እስማማለሁ 42.2% አጠቃላይ ድምራቸው 79.7% ያህሉ በድጋፍ

ሲመለሱ ኣልስማማም 13.3% እና ጭራሽ አልስማማም ያሉት ደግሞ 6.7% አጠቃላይ 20% የሚሆኑት ደግሞ ድጋፍ ማጣታቸው ከጽሁፍ መጠይቅ መረዳት ተችሏል። ስለዚህ ከመረጃው በተገኘው ውጤት መሰረት አብዛኛው ተማሪዎች ምላሽ የሰጡት 79.9% ያህሉ መምህራን በሚጽፎአቸው ጽሁፎች ላይ ስህተቶችን መርጠው እርማት እንዳሚሰጧቸው ለማወቅ ተችሏል።

በተራ ቁጥር 5 ላይ የተብራራው ሀሣብ መምህሬ በምጽፈው ጽሁፍ ላይ ታዩትን ስህተቶቸ በሙሉ ያርሙልኛል በሚለው ላይ በጣም እስማማለሁ ብለው የመለሱ ተማሪዎች የሉም። እስማማለሁ 11.1% አልስማማም 62.2 እና ጭራሽ አልስማማም 26.7 በማለት ገልጸዋል ከእንነዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው 88.9% የሚሆኑ ተማሪዎች በጽሁፋቸው ላይ ስህተቶችን በሙሉ እንደማይታረምላቸው ከሰጡት መልሶች አኳያ ሊረጋገጥ ተችሏል።

በተራ ቁጥር 6 ላይ በተመለከተ መምህሬ ልረዳቸው የምችለውን ምልክቶችን በመጠቆም እርማት ይሰጡኛል በሚለው በጣም እስማማለሁ 35.5%፣ እስማማለሁ 31.1%አልስማማም 24.4% እና ጭራሽ አልስማማም 8.9% ያህል ናቸው አብዛኛው ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች በድምሩ 66.6% የሚሆኑ ድጋፍ ማግኘታቸው ተገልጾል።

በተጨማሪም 66.6% የሚሆኑ ተማሪዎች በጽሁፋቸው ላይ ያለውን ስህተቶች ሊረዱ የሚችሉትን ምልክቶች በመጠቀም ምላሽእንደሚሰጣቸው ከትንተናው ማወቅ ተችሏል። Byrne (1998) እንደገለጹት መምህራን ምልክቶችን ሲጠቀሙ ማን ለማንኛው ስህተት ምልክቱ እንደተቀመጠ በመጀመሪያ ለተማሪዎች ሊያስረዷቸው እንዳለባቸው ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ከጽሁፋዊ ግብረ መልስ አሰጣጥ ስልቶች እንጻር ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የተገኘው መረጃ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት 79.9%፣ ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት 11.1% እና ጠቋሚ የአስተራረም ስልት 66.6% ያህል ምላሽ ተገኝቷል።

ከነዚህም የግብረ መልስ አሰጣጥ ስልቶች ውስጥ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት 79.9% ያህል ነው" ይህም የአስተራረም ስልት ከፍተኛውን መጠን የያዘ መሆኑን ከመረጃው ሊገኝ ተችሏል" አብላጫውን ቦታ የያዘው ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት ቢሆን እንኳን መምህራኑ ጠቋሚ የአስተራረም ስልትንም አብረው እንደሚጠቀሙበት መረጃው ያሳያል። በጣም ዝቅተኛው ቦታ የያዘው ደግሞ ሁሉንም ስህተቶች የማረም ስልት እንደሆነ መረጃው

ይጠቁማል። ይህ የአስተራረም ስልት የሚከናወነው የተወሰኑ ችግሮችን ብቻ መርጦ በማረም ሲሆን ጥቂት ስተቶች የትኩረት አምድ ሆነው ይመረጣሉ። ስህተቶቹ የሚታረሙት አብዛኞቸ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚፈጽሟቸውና የቋንቋ መማርን በሚያደናቅፍ አጠቃላይ ዋና ዋና የጋራ ችግሮች ላይ ብቻ ነው።

በተጨማሪም ለመግባባት አስቸጋሪ ሊሆኑ የሚችሉ ለሁሉም ወይም ለአብዛኛው ተማሪ የጋራ የሆኑ ዋና ዋና ስህተቶችን ማረም የጽሁፍ ስራን ውጤታማ ያደርገዋል ስህተቶችን መርጦ ማረም የሚከናወናው ስህተቶችን ሁሉ የማረም ዘዴ በቋንቋ መምህሩ ላይ የሚፈጠረውን ጫና ወይም ረዥም ጊዜ መሻማት እና በቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚከሰተውን የተስፋ መቁረጥ ስሜት ለመቅረፍ ታስቦ ነው። Byrne 1988:124 Lalande:1982))

ከላይ ከተጠቀሰው ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን ስህተትን መርጦ የማረም ስልት ከፍተኛውን ቦታ መውሰዱን መረጃው የሚጠቁም በመሆኑ ያላቸውን ጊዜያቸውን ሳይሻማና በተማሪዎችም ላይ ተስፋ የሚዘራ እና ወደፊት ጽህፈትን በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲጽፉ የሚያደርግ መሆኑን ትንተናው ያሳያል።

ሰንጠረዥ 5፡ የመምህራን ጽሁፋዊ ግብረ መልስ አሠጣጥ የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ የቀረቡ መጠይቆች

| ተ.ቁ | የቀረቡ መጠይቆች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | አልስማማም | | ጭራሽ ድምር | |
| | | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ | በቁጥር | በመቶ |
| 7 | የመምህሬ ግብረ መልስ በቃላት አመራረጥ፣ በአንቀጽ አከፋፈል፣ በአረፍተ ነገር አመሰራረት ና አወቃቀር በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም እና በፊደላት ግድፈት ላይ ትኩረት ያደረጋሉ | 12 | 26.7 | 23 | 51.1 | 10 | 22.2 | - | - | 45 | 100 |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በጻፍኳቸው ጽሁፎች ላይ እኔ ራሴ ትኩረት እንዳረግ ይገፋፉኛል። | 5 | 11.1 | 8 | 17.7 | 17 | 37.7 | 15 | 33.3 | 45 | 100 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ የምንረዳው መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ እርማት በሚሰጡበት ጊዜ በቋንቋው ቅርጽ ላይ ትኩረት ያደረጉበትን ግብረ መልስ ለማወቅ የቀረበ ጥያቄ ነው።

በተራ ቁጥር 7 ላይ የመምህሬ ግብረ መልስ በቃላት አመራረጥ በአንቀጽ አከፋፈል በአረፍተ ነገ አመሰራረትና አወቃቀር በስርአተነጥብ አጠቃቀም እና በፊደላት ግድፈት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ብሎ በቀረበላቸው መሰረት በጣም እስማማለሁ 26.7% እስማማለሁ 51.1% በአጠቃላይ ድምር 77.8% ያህል አወንታዊ ምላሽ ሰተዋል አልስማማም በሚል ደግሞ 22.2% የሚሆን ምላሽ ሲሰጠው በፍጹም አልስማማም የሚለው አማራጭ ደግሞ መልስ ሣያገኝ ቀርቷል። ስለዚህ

ከመረጃው በተገኘው መሰረት መምህራኑ በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ አብዛኛውን ጊዜ ትኩረት አድረገው የሚሰጡት በቋንቋው ቅርጽ ላይ መሆኑን ያሣያል፡፡

ይህ ቅርጽ ትኩረት ያደረገው ዋና ትኩረቱ በቋንቋው መሰረታዊ ሁኔታ በሰዋሰው ትክክለኛነት በቃላት አመራረጥ  በባለቤት ግስ ስምምነት  በስርአተነጥብ አጠቃቀም በፊደላት አጣጣልና በጠቅላላው ጥምረት ሁኔታ ነው (Hedge :, 1988 Raimes,:1983 Zamel ,1985,keh,1990) እብዛኛዎቹ የቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸው የግብረ መልስ ትኩረት ወጥ እና አንድ የሆነ መመዘኛ የላቸውም፡፡

በተጨማሪም Zamel,1985) ሙሁራን በግብረ መልስ አሰጣጥ ጊዜ አንድ አይነት አሰራር እንደሌላቸው ይገልጻል ተማሪዎች የታልሚውን ቋንቋ ተግባቦታዋ ተግባር ለማለፍ ሰዋሰዋዊ ስርዓቱን በትክክል ማዋቀርና ማፍለቅ በመቻል እና ባለመቻላቸው ላይ አጽኖት በመስጠት እርማት የሚደረግበት ስልት ቅርጽን ሰረት ያደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም የቋንቋው ግብረ መልስ ከይዘት ይልቅ በቅርጽ ላይ ትኩረት ማድረጉ ለመጻፍ ክሂል መሻሻል የተሻለና ትክክለኛ አካሄድ እንደሆ (Lek :1990 Cohen and cavalcant :1990 zamel :1995) ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ ትንተና አገላለጽ የምንረዳው መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የግብረ መልስ አሰጣጣቸው የትኩረት አቅጣጫ የሆነው በቅርጽ ላይ ማተኮራቸውና የተለያዩ የሙሁራኑም ገለጻ ይህ የትኩረት አቅጣጫ ለተማሪዎች በራሳቸው ተነሣሽነትና የተለያዩ ድርሰቶችኝ እንዲጽፉ አና ለመጻፍ ክሂላቸውም መሻሻልና ትክክለኛ አካሄድ መሆኑን ከገለጻው መረዳት ተችሏል፡፡

በጥያቄ ቁጥር 10 ላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በጻፍኳቸው ጽሁፎች ላይ እኔ ራሴ ትኩረት አንዳረግ ይገፋፉኛል፡፡ ብሎ በቀረበላቸው መሰረት በጣምእስማማለሀ 11.1% እስማማለሁ 17.8%፡ አልስማማም 37.8% : ጭራሽ አልስማማም 33.3% በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በተገኘው መረጃ 71.1% አሉታዊ ምላሽ የተሰጣቸው መሆኑን ከመረጃው ትንተና መረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ መምህራኑ የሚጠቀሙት የግብረ መልስ ትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ላይ ራሳቸው ትኩረት የማድረጉ ሁኔታ የሚያሳይ 71.1% ሲሆን አዎንታዊ ገጽታ ደግሞ 28.9% መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

አጥኚዋ ከዚህ ትንተና የተረዳችው መምህራኑ በተማሪዎቻቸው ጽሁፍ ላይ እነሱ ራሳቸው የራሳቸውን ስህተት ለመፈተሸ ተማሪዎቹን እንደማይገፋፉና በራሳቸው ጥረት ችግራቸውን እንዳይፈትሹ የሚያደረጋቸው መሆኑን መረጃው ይጠቁማል፡፡ ይህ በሌላ መልኩ አብላጫውን መምህሩ በተማሪው ጽሁፍ ላይ ትኩረት የማድረጉ ሁኔታ ሲሆን ተማሪው ግን በራሱ ጽሁፍ ላይ ትኩረት የማድረጉ ሁኔታ ውስንነት የታየበት መሆኑ ትንተናው ገለጾአል በሌላ መልኩ በአጥኚዋ ምልከታ መሰረት መምህራን ለተምሪዎችቸው ቀን እና ርዕስን በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ወደ እለቱ ትምህርታቸው በቀጥታ በመግባት ለተማሪዎቹ እድል በመስጠት እንዲጽፉ ደርጋሉ

በተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ የሃሳብ ፍሰትና አደረጃጀት ላይ ትኩረት ማድረጋቸው በተደረገው ምልከታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ ድርሰቶችን እንዲጽፉ እድሉ በተሰጣቸው ጊዜ በራሳቸው ጽሁፍ ላይ እነሱ ራሳቸው ትኩረት አድርገው እንዲመለከቱት አያደረጉም፡፡ በአንቀጽ አጻጻፍ ሆነ በዓረፍተነገር አደረጃጀቱና የሃሳብ ፍልሰቱ እዛው ክፍል ውስጥ መም\/ሩ ብቻ ትኩረት አድርጎ የእለቱ ትምህርት እንዳደሚጠናቀቅ ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጡትን ግብረ መልስ በቃለልም ሆነ ግልጽ በሆነ መንገድ ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ለተምሪዎቻቸው የማየጠቀሙ መሆናቸውን በምልከታው ጊዜ መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው በአብዛኛው መምህራን የተለያዩ የግብረ መልስ ስልቶችን ለመጠቀማቸውን ያሳያል፡፡ የግብረ መልስ አሰጣጡም የትኩረት አቅጣጫው በመምህር ተኮር መሆኑን መገንዘብ ይቻለላል፡፡ ይህ ደግሞ የተምሪዎችን የድርሰት መጽሀፍ ክሂልን ሊያዳብር አይችልም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተማሪዎች በሚጽፉት ድርሰት ላይ የሃሳብ ፍሰቱንና የአረፍተ ነገር አወቃቀሩን ተጠቅመው የመጻፍ ልምምድ እንዲያደርጉ አያበረታታም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት አስራ አንድ ዝግ ጥያቄዎች በተማሪዎች ጽሁፍ መለማመጃ ላይ መምህራን የሚሰጧቸውን ግብረ መልሶችን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ ከቃለ መጠይቅና ከምልከታ የተገኘው መረጃ አንደተቀራራቢነታቸው አስፈላጊው መልስ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ከዚህም በመቀጠል ደግሞ አንድ ክፍት ወይም ነጻ በሆነ ጥያቄ ላይ ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ አስተያየታቸውን ከዚህ በታች ጠቅለል ባለ መልኩ ቅርቧል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 12 ላይ ተማሪዎች ምህራቹህ ለእናንተ ምን አይነት ግብረ መልስ ቢሰጡ ነው አንድ ተማሪ ወደ ፊት ጥሩ ድርሰት መጻፍ ይችላል ብላቹህ የምታመኑት

- በመጀመሪያ ደረጃ የድረሰትን ምንነት በሚገባ ምስረዳት፡፡
- መምህራን ስለ ድርሰት አይነቶች ከተለያዩ አጋዥ መጽሀፍት በማንበብ ጥሩ ልምድ እንዲቀስሙ ማድረግ
- ተማሪዎች በቤተመጽሀፍት በመኘት ጥሩ ደራሲያን የጻፍትን ድርሰት በማንበብ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማረግ
- በምንጽፈው ጽሁፍ ላይ የሰራነውን ስህተት በሚገባ በማሳየት የመጻፍ ፍላጎታችንን በማያዳክም መልኩ ግብረ መልስ ቢሰጡን
- ስዋሰዋዊ ስህተቶችን ስንፈጽም ስሜትን በማይጎዳ መልኩ መልስ ቢሰጡን
- እኛው ራሳችን እኩል ጥንካሬ እንዲኖረን በቃል ግልጽ በሆነ መንገድ ስህተታችንን አስረድተውን ወደፊት ጥሩ ድርሰት መጻእንደምንችል ቢረዱን
- የራስ ተነሳሽነት እንዲኖረን ግድፈቶቻችንን ማረም እንድንችል መንገድ ቢከፈቱልን፡፡
- ለተማሪዎቹ ሙሉ ሃላፊነት በመስጠት ራሳችን ድርሰት እንድንጽፍ ቢያደርጉ
- የተምሪዎችን ስተት ሳይናገሩ ካለፉ በቀጣይ ጽሁፎቻቸው ላይ እንቅፋትና መሰናክል እንደሚሆንባቸው ቢያሳውቁ፡፡
- ምህራን ግብረ መልስ ሲሰጡ ተማሪው ሊረዳው በሚችለው መልኩ ቢሰጡ፡፡
- የሚሰጠው ግብረ መልስ ኣዎንተዊ ገጽታ ቢኖረው ተማሪውን ወደፊት የሚያበረታታ መሆኑን፡፡
- የተለያዩ የህወተወ ገጠመኞችን እንዲጽፉ መገፋፋት፡፡
- በአጠቃላይ ተማሪው በሚጽፈው ጽሁፍ ላይ
- የቃላት አመራረጥ
- የአረፍተ ነገ አመሰራረት
- የስርኣተ ነጥብ አጠቃቀም
- የሃሳብ አቀነጃጀትና አደረጃጀት
- የሃሳብ ፍስት ቅደም ተከተል
- የፊደላት ግደረፈትና የአንቀጽ ኣከፋፈልን ወዘተ በመሳሰሉት ላይ በተገቢው መንገድ ግብረ መልስ ለተማሪው ቢሰጠው ወደፊት ድርሰትን እንዲጽፉ ሊያነሳሳው እና ሊያበረታታው ቃላቶችን ተጠቅመው ቢሰጡ አስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከተማሪው ነጻ አስተያየት አሰጣጥ አጥኚዋ የተረዳችው ተማሪው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን አመለካከቶች መምህሩ ተገቢ በሆነ መንገድ የሚተገብር ከሆነ ተማሪው ወደፊት

በራሱ ተነሳሽነትና ፍላጎት ያለምንም ፍርሃትና ጭንቀት ጥሩ የሆነ ድርሰት መጻፍ እንደሚችሉ ከተሰጠው መረጃ ለመረዳት ችላለች፡፡

ከቃለ መጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከቃለ መጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንደየተቀራራቢነታቸው ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ጋር ተዛምደው ከላይ የቀረቡ ቢሆንም በዛ ውስጥ ያልተካተቱ ቃለ መጠይቅና የክፍል ምልከታ እንደሚከተለው ቀረቧል፡፡ በተማሪዎች የመለማመጃ ጽሁፍ ላይ የሚሰጡ ግብረ መልሶችን በተመለከተ ከመምህራን ቃለመጠይቅና ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ገለጻ፡፡

የጽሁፍ ግብረ መልስ መስጠት ቸል የሚባላው ጉዳይ አያደለም፡፡ ምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት ግብረ መልስ ለተማሪዎች የበለጠ ዝንዛቤ የሚያስጨብጣቸው (መንገድ የሚያሣያቸው) መሆን አለበት Keh (1990-249) እንደ ገለጻው ጽሁፋዊ ግብረመልስ ማንኛውንም ግብአት ለተጠቃሚው አካል መስጠት ማለት ነው፡፡ እንደ hyland (2003:2) mel አገላለጽ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ግብረ መልስ ተማሪው የሚፈለግበትን ነገር እንዲያገኝ ውጤታማ የሆነ የጽሁፍ ግብረ መልስ የሚመለከት ነው፡፡

በተጨምሪም ተማሪዎች በሚጽፉቸው ጽሁፎች ላይ የሚታዩት የሰዋሰው ስህተቶች እንዲያስተካክሉ ምቹ ሁኔታን መፍጠርን በተመለከተ ከምልከታው በተገኘው መሰረት መምህራኑ ተማሪዎች በሚጽፉቸው ጽሁፎች ላይ የሚታዩታን የሰዋሰው ስህተቶች እንዲያስተካክሉ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ላይ ያላቸው እሰታዋጽኦ በጣም ዝቅተኛ ነው እንዲሁም ተማሪው የተሰጣቸውን የተለያዩ ድርሰት ጽፈው በመምጣት በጽሁፋቸው ላይ የታዩትን የሰዋሰው ስህተት ራሳቸው አይተው እንዲያስተክክሉ ምቹ ሁኔታን ሳይፈጥሩላቸው መምህሩ በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ስህተትን በማስተካከል ይመልሳል እንጂ በራሳቸው ጽሁፍ ላይ የሰዋሰው ስህተቱን እንዲያስተካከሉ አያደርጉም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ሃሣቦች መረዳት የሚቻለው መምህሩ ብቻ የተማሪዎቹን ሰዋሰው ስህተት መምህሩ ብቻ አይቶ ማስተካከል አጥጋቢ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ተማሪው በራሱ ስህተት በሚፈጽመው ድረሰት ላይ ካልተረዳው ለጽህፈት መለማመድ ተሳተፎው አናሳ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የመምህራኑ ትኩረት ራሳቸው ስህተታቸውን እንዲያስተካክሉ ሳይሆን መምህሩ በራሱ ስህተቱን ሳይገልጽላቸው ሲተገብሩ ታይተዋል፡፡

በሌላ መልኩ አጥኚዋ በምልከታዋ ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ ድረሰቶችን የዕለት በዕለት ማስታወሻቸው ላይ ጽፈው ራሳቸው ስህተታቸውን እንዳያርሙ ማበረታታትን በተመለከተ ከተደረገው ምልከታ ተማሪው በራሱ ድርሰት ላይ ስህተታቸውን የማረሙ ሁኔታ በጣም ውስን ነው፡፡ ይልቁን የመምህሩ ድረሻ ስህተትን የማስተካከል ረገድ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ነው ይህ ደግሞ ለተማሪው በየእለቱ በማስታወሻው ላይ የተለያዩ ድረሰቶችን እንዲጽፍ እድል እደማይሰጣቸውና ተነሳሽነትን እንደማይፈጥርላቸው ከምልከታው መረዳት ችላለች፡፡

በተጨማሪም ለያንዳንዱ መምህራን ሦስት ሦስተ ጊዜ በተደረገው ምልከታ መሰረት ተማሪዎች የራሳቸውን የኣጻጻፍ ስልት እንዲከተሉ መምህሩ ማበረታታትን በተመለከተ ከተደረገው ምልከታ ተማሪው የራሱን የአጻጻፍ ስልት እንዲከተል የማድረጉ ሁኔታ በመጠኑ ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ በብዛት ጽፈው እንዲመጡ የሚደረገው በመምህሩ ትዕዛዝ (ፍላጎት) ላይ አብላጫ መሆኑን ተረድታለች፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪው በራሱ ፍላጎት የተለያዩ ድረሰቶችን ጽፎ እንዳይመጣ የታቀበ ይሆናል፡፡

በሌላ መልኩ የተምሪዎችን ስህተት በመለየት የትኛውም ግብረ መልስ አይነት አሰጣጥ ለመጻፍ ክሂላቸውን መሻሻልና ውጤታም ሊያደርጋቸው የሚችለውን ስልት በመግለጽ ዙሪያ በተመለከተ በምልከታ የተገኘው መረጃ መምህሩ ወደ ክፍል በሚገባበት ወቅት ለተማሪው ርዕሱን ሠሌዳ ላይ በመጻፍት ድርሰት እንዲጽፉ ያደርጋሉ ነገር ግን በተጻፈው ድርሰት ላይ የተለያዩ ግብረመልሶችን በመስጠት የትኛው ለመጻፍ ክሂላቸው መሻሽል እና መዳበር ወይም ውጤታማነት ሊያደርጋቸው የሚችለውን ስልት በመግለጽ አኳያ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ተገንዝባለች፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎቸሁ በራሳቸው ስህተታቸውን አውቀው እንዲያስተካክሉና በጻፉት ጽሁፍ(ድርሰት) ላይ ለማሻሻላቸው የሚጠቀሙትን የግብረ መልስ አይነት ግልጽ እና ይፋ ሆኖ ለተማሪው እንደማይነገር እና እንደማይገለጽለት ከምልከታው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ከምልከታው በተገኘው መረጃ መሰረት በተመለከት ተማሪዎች የጻፍትን ድርሰት እርስ በርስ እርማት እንዲሰጣጡ በምድረግ ረገድ ያለው ሚና ከተማሪዎች የቤት ስራ እና ደብተር ምልከታ አጥኚዋ የተረዳችው በብዛት ተማሪዎች ከግል እና ከመምህሩ እርማት ይልቅ የቢጤ (እርስ በርስ) እርማት እንደሚያስደስታቸው ተረድታለች ምክናያቱም የሚጽፉትን

ድርሰት እርማቱን ሲሰጡ ያላቸው አመለካከት ከነጥብ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ደስተኛ ደርጋቸዋል። ከዚህ ምልከታ ደግሞ መረዳት የተቻለው መምህሩ የቢጤ እርማት እንዲያደርጉ ከማበረታታት ይለቅ በድርሰታቸው ላይ ራሱ መምህሩ እርማቱን ሲሰጥ ተስተውሏል። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹን ደስተኛ እንደሚያደርጋቸው ታይቷል።

Hillocks (1986፡240) እንደሚገልጹት ከመምህር ድጋፍ በተጨማሪ የአቻ ለአቻ (የቢጤ) እርማት ቢጨመር በተናጥል ከተደረገው እርማት ይበልጥ ውጤታማ እንደሆና እና ተማሪዎች በእርማት ወቅት ከጓደኞቻቸው ጋር በመረዳዳት በድርሰቶቻቸው ወይም በወረቀቶቻቸው ላይ እርማትም ሆነ አስተያየት እየተሰጣጡ እንዲለማመዱና እንዲጽፉ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል።

በአጠቃላይ ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት ከመምህራቸው ከሚሰጣቸው አስተያየትና እርማት ይልቅ ትኩረታቸው በሚሰጣቸው ነጥብ ላይ ስለሆነ ስለ ጽህፈቱ ትክክለኛነት ትኩረት እንደማያደርጉ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም መምህራን እርማት እና አስተያየት መስጠታቸው እንዲሁም የተማሪዎችን ጽሁፍ ከውጤት ጋር ማዛመዳቸው ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል እንዲያዳብሩ አያደርጋቸውም። በጥያቄ 1 ለተማሪዎች የሚሰጡ ጽሁፋዊ ግብረ መልስ በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ(ድረሰት) የመጻፍ ችሎታቸውን ያሻሽላል ብለው ያምናሉ ብሎለቀረበላቸው ጥያቄ በተመለከተ መ.1. የሰጡት ምላሽ ከዚህ በታች ይሆናል። ለቃለ መጠይቁ ምላሽ ከመስጠታቸው በፊት ስለ ጽህፈት ክሂል አንዳንድ ማብራሪያዎችን ሰተዋል ይህም ማብራሪያ የጽሁፍ ክሂል በቀላሉ የሚጨበጥ ክሂል አይደለም። የጽህፈት ክሂል ውስብስብና ረቂቅ የሆነ ክሂል ነው። በተለይ ደግሞ አስቸጋሪነቱን የሚያሳየው እንደማዳመጥና መናገር በልምድ ሳይሆን በትምህርት ብቻ የሚገኝ መሆኑ ነው። የጽህፈት ክሂል በትምህርት ውስጥ ውሰወብስብና አስቸጋሪ የሚያደርገውም" በውስጡ ከሰዋሰዋዊ ጉዳዮች በተጨምሪ የግንዛቤን ፡ የአስተውሎትንና የማመዛዘንን ችሎታ የመጠየቁ ጉዳይ ነው።

ስለዚህ አንድ የተዋጣለት ጽሁፍን አጠናክሮ ለማቅረብ ብዙ ነገሮችን ማወቅ ይጠይቃል"

በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ

- ሃሳብንና መረጃዎችን አቀናጅቶ አጠናክሮ ማቅረብ
- ከአሻሚነት ነጻ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ማቅረብ

- ለአጽንኦት ሲባል ውስብስብ ያሉ ሰዋሰዋዊ ስርአቶችን መጠቀም
- ጥያቄ የተሞላበትን የቃላት ምርጫና አጠቃቀምን መከተል
- ተገቢውን የሰዋሰው አጠቃቀም መከተልና የዐረፍተ ነገር መጠን ማወቅ ናቸው፡፡

በመጨረሻም ለማብራራት የምፈልገው የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ሲዘጋጁ በእነዚህ ነጥቦች ላይ ማትኮር ይገባል፡፡ እነዚህን ነጥቦች ለመጥቀስ ያህል የጽፈት ክሂል መልመጃዎችን ተግባራዊና ጠቃሚ በሆኑ የጽህፈት አይነቶች ላይ ማትኮር ይኖርብናል፡፡

በመቀጠልም የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች የሚያተኩሩበት ልምምድ ተግባራዊ ወይም አግልግሎታዊ መሆን አለበት በተጨማሪም ደግሞ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ሰዋሰውና ቃላትን ለማስተማር መርዳታቸው ጎን ለጎን ሌሎች ክሂሎችንም ለማሳደግ የሚረዱ መሆን አለባቸው መ.1 ለጥያቄ ቁጥር 1 የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ይሆናል አዎን ምንያቱም ጽሁፋዊ ግብረ መልሶችን የተማሪዎችን የጽህፈት ችሎታቸውን በይበልጥ የሚያዳብርላቸው በመሆኑ ድርሰት ከአእምሮአቸው አፍልቀው እንዲጽፉ በማድረግ የመጻፍ ችሎታቸውን ያሻሽላል፡፡ መ.2 ለጥያቄ ቁጥር 1 የሰጡት ምላሽ የሚሰጠው ግብረ መልስ በመልስነት ደረጃ ለአነድ ነግር ብቃት እንደሚኖረው እና ለተማሪዋች የመጻፍ ችሎታን እንደሚያሻሽል የታወቃ ነው ነገር ግን ድርሰት ለመጻፍአስተዋጽኦ ይኑረው እንጂ ድርሰትን የመጻፍ ችሎታቸውን የማሳደግ ብቃቱ ብዙም የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ጥያቄ ቁጥር 3 ለተማሪዎች ምን ኣይነት ግብረ መልስ ቢስጥ ነው በመጻፍ ችሎታቸው ላይ መሻሻል የሚያመጡት ትላላቹህ በሚለው ጥያቄ በተመለከተ መ.1 የጽህፈት ክሂል መለማመጃ መልመጃዎችን በማቅረብ ተማሪዎች በሚጽፉት የጽሁፍ አይነት ከቅርጽ እና ከይዘት አደረጃጀት ጋር በበቂ ሁኔታ መተዋወቅ መቻላቸውን በሚገባ ካረጋገጥኩኝ በኋላ አደርጋለሁኝ በመጨረሻም ወጤት ላይ እንዲደርሱ ተማሪዎች የጎደለውን ነገር ለመሙላትና አደረጃጀትን ከማስተካከል አልፈው ከራሳቸው በማፍለቅ ወጥ ጽሁፍ እንዲያዘግጁ አደርጋለሁኝ፡፡ ለምሳሌ በትውውቅ ደረጃ ከደብዳቤ አጻጻፍ ጋር ተዋውቀው በተከታዩ ደረጃ ደግሞ ለፈለጉት አላማ ሊውል የሚችል የተሟላ ደብዳቤ ስርአቱን በመጠበቅ ከራሳቸው አፍልቀው በመጻፍ ለውጥ እንዲያመጡ አደርጋለሁ፡፡ የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡

መ.2. ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር እንዲችሉ መሰጠት ያለበት ግብረ መልስ ጽህፈትን በመጻፍ እንዲዳለማመዱና እንዲያዳብሩ የተለያዩ ነገሮችን እንዲጽፍ በማድረግ በመጻፍ ችሎታቸው ላይ ለውጥ እንደሚያመጡ ይገመታል ብለው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4 የተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ ጽሁዊ ግብረ መልስ ወይም እርማት ሲሰጡ በብዛት የትኛውን አይነት ጽሁፋዊ ግብረ መልስ ይጠቀማሉ ለሚለው የተሰጠው ምላሽ መ.1 እርማቱን ከጽሁፋቸው አኳያ በማረም የጽህፈት ክሂልን ለመመዘንና ለመገምገም ከፍተኛ እገዛ የሚያደርጉትን ነጥቦች በጥንቃቄ በመጠቀም ማለትም በማግባባት ብቃቱን በማጤን እንዲሁም በተጠየቃዊ አደረጃጀቱ ና በቅረጽና በአቀራረቡ ምን መልክ እንደያዘ መረዳትን በሰዋሰው ቅንብር ደረጃውን በመፈተሽ እንዲሁም በእጅ ጽሁፍ በስረዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና በመሳሰሉት መስፈርቶች የጽህፈት ክሂል በመመዘንና በመገምገም አከናውናለሁኝ፡፡ ለምን ለሚለው ጥያቄ በትክክል ግምገማውንና እርማቱን ለማከናወን ስለሚያስችሉ ነው፡፡

መ.2 በጽሁፍ መለማመድ ረገድ በጣም ጠቃሚ የሚሆነው ግብረ መልስ የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የሚረዳቸው ጽሁፋዊ ግብረ መልስ መጠቀሙ የተሻለ ነው ለምን ቢባል በጻፉት ነገር ላይ እርማት ሲሰጥ ይህንን እንደዚህ አድርገው ይህ ጥሩ ነው በዚህ ቀጥል ወዘተ እያልኩ ምክሬን በመለገስ ስከታተላቸው በፊደል ኣጻጻፋቸው ረገድ የሚወሰወዱትን የአጻጻፍ ስልት የበለጠ ይረዳቸዋል፡፡ በማለት መልስ ሰተዋል ጥያቄ ቁጥር 5 ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መሻሻል ውጤታማ ሊያረጋቸው የሚችለው የጽሁፍ ግብረ መልስ አሠጣጥ ስልት ምን መሆን ኣለበት ይላሉ ለምን መ.1 በእኔ አመለካከትና አተያይ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎችን በተገቢው መንገድ ማዘጋጀት ግድ ይላል፡፡ ይህ ሲሆን የመልመጃዎቹን ውጤታመነት ከፍ ያደርጋል፡፡ ከእነዚህ ነጥቦች በተጨማሪ መልመጃዎቹ ሲዘጋጁ ተከታዮቹን ዝርዝር ጉዳዮች በተንዳኝ ማጤን ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት የሚዘጋጁ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች በቡድን ሆነው በውይይት የሚሰሩ ቢሆኑ የተሻለ ነው፡፡ እላለሁ ምክንያቱም እንዲህ ያለ መንገድ አንዱ ከሌላው መማር እንዲችል እድል ከመፍጠሩም በላይ ጽህፈት ጎን ለጎን የመናገር የማዳመጥን እና የማንበብ ችሎታን አቀናጅቶ ለማዳበር የሚረዳ ነው፡፡ ሌላው መዘጋጀት ያለበት የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ለተማሪዎች ስሜትና ፍላጎት የቀረቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል በመቀጠልም የሚዘግጁት የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ተመጥነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ሲባል በጣም ቀላል ወይም ከባድ መሆን የለባቸውም ለማለተ ፈልጌ ነው ስለዚህ ለተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል መሻሽልና ውጤታማ የማድረጊያ አንዱ ዘዴ ነው ባይ ነኝ፡፡

በመጨረሻም የማነሳቸው ነጥቦች ቢኖሩ የሚዘጋጁት የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች የተማሪውን ዕድሜ ፡ ብስለትና የትምህር ደረጃ ያገናዘቡ መሆን ሲኖርባቸው የጽፈት ክሂል መልመጃዎች ተማሪዎቹን ከተለያዩ የጽህፈት ክሂል ጋር የሚያስተዋውቁ መሆን ይጠበቅባቸውል፡፡

በመሆኑም ማቅረብ የሚገባው መልመጃዎች የግል ጹሁፎችን፣ ማህበራዊ ጹሁፎችን፣ ኪናዊ ጹሁፎችን፣ ጥንታዊ ጹሁፎችን እና ተቋማዊ ጽሁፎችን ያካተቱ ሊሆኑ ይገባል የሚል ሃሳብ አለኝ ለምን ለሚለው እነዚህን በዝርዝር ያስቀመጠኳቸውን ምላሾች የተማሪውን የመጻፍ ክሂል በሚገባ የሚያሻሽል ውጤታማ ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ" መ.2 ለተማሪዎች መሻሻልና ውጤታማነት የተሻለ ነው ብዬ የማስቀምጠው ሃሳብ በተማሪዎቹ የመጀመሪያ አጻጻፍ ላይ የተሻለና የተመረጠ የሚሆው ግብረ መልስ በምንሰጥበት ጊዜ ኣብዛኛውን ጊዜ ካለ ግራፍ ነው፡፡ ይህ ማለት ካገኙት ግብረ መልስ ያለምንም ስህተት ራሳቸውን አውቀው መጻፍን ማዳበር ስለሚችሉ ነው፡፡ በተጨማሪም የመጻፍ ክሂል መሻሻልና ውጤታማ መሆን የሚያችለው በድግግሞሽ የመጻፍ ሁኔታ መኖር ነው ለምን ለሚለው ጥያቄ ተማሪዎች በደግግሞሽ ግብረ መልስ ሲሰጣቸው ምን አይነት ስህተት በጽሁፋቸው ላይ እንዳደሰሩ በተደጋጋሚ በማየት ራሰቸውን ወደ ማስተካከልና በራሳቸው ተነሳሽነት ወደ መጻፍ ያመራሉ ባይ ነኝ በተጨማሪም ከዓረፍተ ነገር አወቃቀር እስከ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ድረስ ያለውን ስህተት በመደጋገም በማሳየት ኣስተካክለው እንዲጽፉና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል በማለት ምላሽ ሰተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው መምህራኑ በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚጠቀሙት (የሚሰጡት) የተለያዩ የግብረ መልስ አይነቶች ላይ ትኩረት እንደሚያደረጉ በቃለ መጠይቁ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

በጥናቱ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሁፍ መለማመጃቸው ላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሰጧቸው የግብረ መልሶች ትንተና የሚል ነው፡፡ በዚህም በጽሁፍ መለማመጃቸው ላይ የጽህፈት ክሂልን ለማዳበር እና ለማሳደግ የመምህሩ የግብረ መልስ አሰጣጥ ከተማሪዎች ችሎታ ጋር ያለውን ግኑኝነት በመፈተሽ ክፍተት ካለ ማቀራረብ የሚያስችል ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡ በዚህም ፍተሻ በተገኘው ውጤት ቀጥሎ ለቀረቡት ዝርዝር ዓላማዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው ድርሰት ላይ ጽሁፋዊ ግብረ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ምን አይነት ግብረ መልስ እንደሚጠቀሙ መመርመር፡፡
2. ተማሪዎች ለጻፋቸው ድርሰቶች ግብረ መልስ ሳያገኙና ካገኙ በኋላ ያለውን ልዩነት መፈተሽ
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚጠቀሟቸውን የግብረ መልስ ስልቶችን መለየት እና
4. መምህራኑ በተማሪዎች ድርሰት ላይ የሚጠቀሙትን ግብረ መልስ ዎንታዊና አሉታዊ ገጽታ መለየት፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ በመጀመሪያ ተጠኚዎችና የመረጃ መሣሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ ተጠኚዎች በ2015ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን ይህ ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩ መምህራን ደግሞ በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ከጥናቱ አላማ ጋር ትስስር ያላቸው ንድፈ ሃሳቦች በምዕራፍ ሁለት ተገልጸዋል፡፡ በምዕራፍ ሦስትም የአጠናኑ ሁኔታ ተገልጾአል" የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹም ምልከታ የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ መሆናቸውን የአተናተን ዘዴውም ማብራሪያ ተሰቶበታል በዚህ መልኩ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነታዊ በመጠናዊ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር አላማዎችን በተመለከተ በተካሄደው ጥናት መሰረት የተገኘውም ውጤትም እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ተማሪዎች ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና በተለያየ ደረጃ ግንዛቤአቸውን እንዲያሰፉ እና የተለያዩ ድርጊቶችን እንዲያዳብሩ እንዲሁም የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ግብረ መልስ መስጠት ይጠቅማቸዋል፡፡ ከዚህም እንጻር መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የግብረ መልስ አይነቶችን በመጠኑ እያሰባጠሩ ቢጠቀሙም ከፍተኛውን ቦታ (መጠን) ይዞ የተገኘው አስተካካይ ግብረ መልስን አዘውትረው መጠቀማቸው የጥናቱ መረጃ ያሣያል አስተካካይ ግብረ መልስን በሚሰጥበት ጊዜ መምህራን በተማሪዎቻቸው ጽሁፍ ላይ የቃላት · የአረፍተ ነገር ቅደም ተከተል ከተዛነፈ በድጋሚ በመጻፍ እና ምልክት በማድረግ እንዲሁም አያያዥና ስርዓተ ነጥቦችን ካለ በመጨመር ማስተካከል ተመራጭ ይሆናል" Lind Man(1995) ከዚህ ምሁራን ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊነት ይታይበታል፡፡

በሌላ መልኩ በአጠኚዋ በተደተገው ምልከታ ተማሪወች በጻፍት ጽሁፍ ላይ የአንቀጽ አደረጃጃት ላይ ራሳቸው ትኩረት እንዲያደርጉ የማድረጋቸው ሁኔታ ውስንነት የታየበት ነው ነገር ግን መምህራኑ በተማሪዎች ወረቀት(የቤት ስራ) ላይ የጎደለውን ስርዓተ ነጥቦች በመጨመር የማስተካከል ሁኔታው ጥሩ ጎን የታየበት ሲሆን በደብተራቸው ላይ ግን በየጊዜው በጻፍት ጽሁፍ ላይ ትኩረት ሠቶ ማስተካከሉ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ በቡድን እንጂ በየግላቸው የመጻፍ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ማድረጉ ከመረጃው ሊገኝ ችሏል፡፡

መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ አስተያየት ሲሰጡ አወንታዋና አሉታዊነት. ባህሪ የተላበሱ ናቸው ይሁን እንጂ አወንታዊ ባህሪ ያላቸውን ግብረ መልስ በብዛት መጠቀማቸውን ከጽሁፍ መጠይቁና ከቃለመጠይቁ በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል ይህ ደግሞ የተማሪውን የመጻፍ ችሎታ ያሳድጋል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ምክንያቱመቱም አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ግብረ መልስን በተገቢውና ሚዛናዊነቱና በጠበቀ መልኩ ቢስጥ የተሻለ እንደሆነ Coll and Chain {1994:225} ከሚለው ከሙሁራን ሃሳብ ጋር ይጋጫል፡፡ ስለዚህ ሁለቱን እያሰባጠሩ መስጠር ጠቃሚ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ የግብረ መልስ ኣሰጣጥ ስልቶችን በተመለከተ መምህራን የሚሰጡት ግብረ መልስ ሁሉንም የማረም ስልት ቢጠቀሙም አብላጫውን ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት እንደሚጠቀሙ ከጽሁፍ መጠይቁ በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ስህተቶችን መርጦ የማረም ስልት በቋንቋው መምህር ላይ የሚፈጥረውን ጫና(ረጅም ጊዜ) መሻምትን በቋንቋው ተማሪዎች

ላይ የሚከሰተውን የተስፋ መቁረጥ ስሜት ለመቅረፍ ታስቦ ነው Byrne 1988:124: Lalande :1982): ከሙሁራኑ እሳቤ ጋር ውጤቱ መደጋገፉ ታይቷል፡፡

መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚጠቀሙትን የግብረ መልስ የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅና ከምልከታው የተኘው መረጃ የመምህራኑ የትኩረት አቅጣጫ በቅርጽ ላይ መሆኑን መረጃው ያሠያል፡፡

ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ መረዳት እንደሚቻለው ለተማሪዎች ምን አይነት ግብረ መልስ ቢሰጥነው በመጻፍ ችሎታቸው ላይ መሻሻልን የሚያመጣው ለተማሪው በተደጋጋሚ በክፍልም ሆና በውጭ የተለያዩ ድርሰቶችን የግል ገጠመኞቻቸውን ጽፈው ቢመጡና አወንታዊ ምላሽ ቢሰጣቸው መሻሻልን እንደሚያመጡ መረጃው ይጠቁማል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን አብዛኛውን አስተካካይ ግብረ መልሶችን መጠቀማቸው የሚጠቀሙትን ምልክቶች ተማሪዎች በጽሁፎቻቸው ላይ ይረዱታል አይረዱትም የሚለውን ከግምት ውስጥ አለማስገባታቸው አወንታዊ ግብረ መልስን ማዘዋተራቸው እና የግብረ መልስ ስልቶችን እያቀላቀሉ ቢጠቀሙም አብዛኛውን ግን ስህተትን መርጦ የማረም ስልቶችን መጠቀማቸው ከይዘት ይልቅ ቅርጽ ላይ ትኩረት ማድረጋቸው በተማሪዎች ድርሰት አደረጃጀትና ቅደም ተከተል ላይ ትኩረት አድርገዉ የግብረ መልስ አሰጣጣቸው የተሻለ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

## 5.2. አስተያት

የጥናቱ ውጤት መሰረት በማድረግ በጥናቱ ማጠቃለያ ለቀረቡት ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ ብላ ያሰበችውን አስተያቶች በአጥኚዋ አቅርባለች፡፡

- የቋንቋ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት አስተካከይ ግብረ መልስን ነው፡፡ አንዱን ብቻ በአብላጫው ከመጠቀም የግብረ መልስ አይነቶችን ምንነታቸውን በማሳወቅ እያጣመሩ ቢጠቀሙና አስተካካይ ግብረ መልስ ሲሰጡ ደግሞ ግልጽ በሆኑ ቃላትና ተማሪዎች መረዳት በሚችሉ መልክ ቢሆን ይመረጣል፡፡
- በተማሪዎች ጽሁፎች ላይ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ስለሚቻል ሁሉንም የግብረ መልስ ስልቶች እንደ አስፈላጊነታቸው እያጣመሩ ቢጠቀሙ እና የትኛው ምልክት ለየትኛው ስህተት እንደተቀመጠ ግልጽ በሆነ መልኩ ቢቀመጥ፡፡

- ተማሪዎቹ በራሳቸው ተነሳሽነት ፍላጎት እንዲጽፉ ቢደረግ በመምህሩ ግፊትና አስገዳጅ ባይሆን፡፡
- የቋንቋው መምህራን በአብዛኛው አዎንታዊ ግብረ መልስ ብቻ ሳይሆን አሉታዊውንም እያሰባጠሩ ቢጠቀሙ፡፡
- መምህራኑ ለተማሪዎቻች የጽሁፍ ግብረ መልስ መስጠታቸው ጠቀሜታ አላማ አተገባበር ለተማሪዎች ግንዛቤ ቢሰጣቸው፡፡
- የቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የጽሁፍ መለማመጃ ላይ በጥልቀት በማንበብና በመረዳት ተገቢውን ግብረ መልስ ቢሰጧቸው፡፡
- በአጠቃላይ መምህራን የሚሰጣቸው ጽሁፋዊ ግብረ መልስ በቋንቋ አጠቃቀም በይዘት አደረጃጀት በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይ ያለ መሰላቸት ትኩረት ቢሰጣቸው፡፡

## ዋቢ መፃህፍት


ማረው አለሙ፡፡ (1987) "በኢትዮጵያ ቋንቋችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል ለሁለተኛ አመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚፃፍ በሣልድርሰቶች ንፅፅራዊ ግምገማ ጥናት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ የቀረበ፡፡(ያልታተመ)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996) "በስነ ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፡ ንግድ ማተሚያ ድርጂት፡፡

ባዬ ይማም፡፡ (1987) የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ ት.መ.ማ.ማ.ድ

ትግዕስት ታረቀኝ፡፡(1998)፡፡ "በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የበሳል ድርሰት መምህራን የፅሁፍ ምጋቤ ምላሽ ትኩረት ፍተሸ" ድህረምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲት/ያልታተመ/

እንዳለ ተስፋዬ፡፡ (1992) "በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ ሚና፡፡" ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ ኣዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ/የልታተመ/

እታለማሁ ታዬ፡፡ (2006)፡፡ "የ9ኛ ክፍል የአማርኛ  ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የጽሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጡት ጽሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ፤ በየካቲት 23 2ኛ ደረጃ ተ/ቤት ተተኳሪነት፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣በአማርኛ ማስተማር ለኤም.ኤ. ድግር ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡(ያልታተመ)፡፡

እጅጋዬሁ በቀለ፡፡ (2011)፡፡ "በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ምጋቤ ምላሽ የለው አሰተዋፅኦ ትንተና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡" በጅማ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የቀረበ ጥናት/ያልታተመ/

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2001)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ ን.ማ.ድ፡ አዲስ አበባ፡፡

Anglo, T.A. and Crass, P.K (1993). Class room Assessement Techique: A Hand book for college teachers. Sanfrancisco: bass L.t.f

Anker, W. (2000)."Error and corrective feedback: to theory and class room practice." Forum 38(4), 21-24.

Byren, D. (1988) Teaching English writing. Landon: long man, Keh, C.L. (1990), "Feedback In The writing process, A model and method for Implementation." *ELT Journal, 44(4) ፣294-304.*

Candan, W. and W. Butler. (1997). Writing the information super high way, Bostan: A Via company.

Chaudran, C, (1984) “The Effect of feedback and students composition Revision” RELC.

Colle, P.G. and Chan, L.K. (1994).Teaching principles and practice. Australia: Mc phersan’s printing group.

Cohen .A.D & Cavalcant.M.C.(1990) Feedback.one ceompositins teachers and students verb al reports. In.B.Kroll (ed). Second language. Wrighting.cambridge Unvesity press.

Daiker, D.J. (1989). Writing and Respanse: Theory, Practice and Research. NJ: Hamptan.

Daiker, D.J. (1989). Writing and response: Theory, practice and Research. NJ.

Duker, H. (1983) writing through sefuence: A process Approach. Oxford: oxford university press.

Fregeav, L.A.(1999) “Preparing ESL Students for college writing Two case students.” *The internet TESL Journal; vol. V No. 10 http// iteslj.org/.*

Griwin, T. (1991) “Giving students the right ideas: away to provide feedback on writing.” English Teaching forom. 29/3:2-5 Hamptan.

Harmer, T. (1991).The practice of English Language Teaching. Landon: Long man Anglo, T.A. and crass, P.K(1993). Class room Assessment Techique: A Hand book from college teachers. Sanfracisco: bass L.t.d.

Heaton, J. (1988), Writing English Laguage Tests. Longman Group Limited, New York. U.S.A.

Hedge, T. (1988) writing oxford; oxford university press.

Hyland, K. (1990) “Providing productive feedback” ELT *Journal. 44/y: 279:285*

Hyland , K(2003) second language wrighting . Hong Kong: Cambrage Unversity Press.

Hill , J.(1986).teaching literature is the language class room. London: Macinillial publish

Jacobs, H. and *et.al.,*(1981), Testing ESL composition: A practical Massachusetts: New bary House publishers.*Journal, 1s/z:* 1-4.

Key, C.L (1990) “Feedback in The Writing Process, A Model and method for Implimenatatian” ELT *Journal, 44(4), 294-304.*

Laland, J. (1982). “Reducing composition Errors an Experiment.”Modern Language J*ournal, 66(2) 140-149.*

Leki, I. (1990) “Coaching from the margin: Issues in written response.” In B. Kroll(ed) second Language writing: Research in sight for the classroom. Cambridge: Cambridge university press.

Lind Mann, E. (1995). A. Rhetoric for writing teachers. Oxford: oxford university press.

Moxely, J. (1989). “Responding to student writing: Goals, method and Alternatives.”Fresh man English news, 17 (2), 3-11.

Moxely, J. (1989). “Responding to student writing: Goals, method and Alternatives.”Freshman English news, 17(2), 3-11.

Owens ,L.R.G. Straton.(1990)” The development of comparative , compitative and individual learning refarnce scale for students . “ In British jornal of education Psycology . 50/2:147-161

Pincas, A. (1982) Teaching English writing Landon; macmill an publishers.

Porto, M. (2000) “Cooperative writing Response Groups and self- Evaluation.”*In ELT Journal ss/1:38-46.*

Raimes, A. (1983). Techniquesin Teaching Writing. Oxford: university press.

Ur, P. (1996), A. course in Language Teaching: practice and theory. Cambridge: Cambridge University press.

Widdowsan, H.G. (1978). Teaching Language communication: oxford; oxford University press

Zamel, V. (1985) “Responding to student writing” TESOL Quarterly. 21: 697-715.

Zamel, V. (1982).”Writing.The process of discovering meaning.”In TESOL Quarterly vol. (691) 195-209.

# አባሪዎች

# አባሪ1

**ለመረጃ መሰብሰብያ የተዘጋጄ ጥያቄዎች**

**ለተማሪዎች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**ድህረ ምረቃ መረሀ ግብር**

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍ ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

በተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

**ዉድ ተማሪዎች**

የዝህ ፅሁፍ መጠይቅ ዋና አላማዉ የመምህራን ግብረ መልስ ወይም የመምህራን እርማት አሰጣጥ በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ ምን ጥቅም እንዳለዉ መረጃ ለመሰብሰብ የታሰበ ነዉ።

በመሆኑም ጥናቱ ከግብ ይደርስ ዘንድ የናንተ ቀናና ትክክለኛ መልስ ለጥናቱ ዋና መሰረት መሆኑን እየገለፅኩ ለምትሰጡት ትክክለኛ ምላሽ በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

**ማሳሰቢያ**

በፅሁፍ መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም።

ጥናቱ የየግላችሁን ምላሽ ስለሚፈልግ በጋራ መስራት አያስፈልግም።

አጠቃላይ መረጃዎች

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በክፍት ቦታ ላይ ምላሻችሁን ፃፉ።

ፆታ..........................

ዕድሜ.......................

የክፍል ደረጃ.........................................

የትምህርት ቤት ስም..........................................................................

ከዚህ በታች ለቀረቡት እያንዳንዱን ጥያቄ በጥሞና ካነበባችሁ በኃላ የናንተን ሀሳብ የሚገልፁትን አንድ ምርጫ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመምረጥ በጣም እስማማለሁ(4) ፣ እስማማለሁ(3)፣ አልስማማም(2) እና ጭራሽ አልስማማም(1)"x"በማድረግ መልሱ።

| ተ.ቁ | የቀረቡትጥያቄዎች | ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ ለምፅፈው ፅሁፍ የሚሠጡኝን ግብረ መልስ ቶሎ በመረዳት አስተካክላለሁ፡፡ | | | | |
| 2 | በፃፍኳቸው ፅሁፎች ላይ መምህሬ ምንም አይነት ግብረ መልስ ሣይሰጡኝ ሙሉ ነጥብ ያስቀምጡልኛል፡፡ | | | | |
| 3 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በምፅፈው ፅሁፍ ላይ የፅሁፍ ግብረ መልስ በመስጠት በሀሳብ አደረጃጀትና ቅደም ተከተል ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በፅሁፍ ላይ የሚታዩትን ስህተቶች ብቻ መርጠው ግብረ መልስ ይሰጡኛል፡፡ | | | | |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ በምፅፈው ፅሁፍ ላይ የታዩትን ስህተቶች ሁሉ ያርሙልኛል፡፡ | | | | |
| 6 | መምህሬ ልረዳቸው የምችለውን ምልክቶች በመጠቀም ምጋቤ ምላሽ ይሠጣሉ፡፡ | | | | |
| 7 | የመምህሬ ግብረ መልስ በቃላት አመራረጥ፣በአንቀፅ አከፋፈል፣በአረፍት ነገር አመሠራረት፣በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና በፊደላት ግድፈት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ መምህሬ የሰጡኝ ግብረ መልስ በቀጣይ ለምፅፈው ፅሁፍ ምንም አይነት ድጋፍ አላደረገልኝም፡፡ | | | | |
| 9 | የመምህሬ ግብረ መልስ ወደፊት ለምፅፈው ፅሁፍ ፍላጎት አሣድሮብኛል፡፡ | | | | |
| 10 | የምፅፏቸው ፅሁፎች ሣልዘነጋቸው ቶሎ ታርመው ይመለሱልኛል፡፡ | | | | |
| 11 | መምህሬ የሚሠጡኝ ፅሁፋዊ ግብረ መልስ አወንታዊ ገፅታዎች አሏቸው፡፡ | | | | |

**ክፍት ጥያቄ** 12. መምህራችሁ ምን አይነት ግብረ መልስ ቢሰጡ ነው አንድ ተማሪ ወደፊት ጥሩ ድርሰት መፃፍ ይችላል ብላችሁ ታምናላችሁ?

## አባሪ 2

**ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ**

**ለመምህራን የቀረበ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች**

**አጠቃላይ መረጃ**

1. የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት-------------------------------
2. የሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ -----------------

**አጠቃላይ ጥያቄዎች**

1. የሚሠጡት ፅሁፋዊ ግብረ መልስ ለተማሪዎች የፅሁፍ መለማመጃ ላይ /ድርሰት/ የመፃፍ ችሎታቸውን ያሻሽላል ብለው ያምናሉ?
2. ተማሪዎች አጠቃላይ ግብረ መልስ ከማግኘታቸው በፊትና በሁዋላ በመፃፍ ችሎታቸው ላይ ልዩነት /ለውጥ/ ያለ ይመስሎታል?
3. ለተማሪዎች ምን አይነት ግብረ መልስ ብሰጥ ነው በመፃፍ ችሎታቸው ላይ ለውጥ የምያመጡት ትላላችሁ?
4. የተማሪዎች የፅሁፍ መለማመጃ ላይ ፅሁፋዊ ግብረ መልስ ወይም እርማት ሲሰጡ በብዛት የትኛውን አይነት ፅሁፋዊ ግብረ መልስ ይጠቀማሉ? ለምን?
5. ለተማሪዎች የመፃፍ ክሂል መሻሻልና ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚችለው የፅሁፍ ግብረ መልስ አሠጣጥ ስልት ምን መሆን አለበት ይላሉ? ለምን?

**አባሪ 3**

## 7. የምልከታ ቅጽ

የዚህ የምልከታ አላማ በደብረ ጽጌ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ላይ የሚታየውን በተማሪዎች የጽሑፍ መለማመጃ ላይ መምህራን የሚሰጡትን ግብረ መልስ ለችግሩ መፍትሄ ይሆን ዘንድ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ከዚህ ጥናት ለሚገኘው ውጤት ለመፈለግ ላይ ላለው ዘዴ ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ስለዚህ በቃለ መጠይቁ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል ናቸው ብላችሁ የምትገምቷቸውን መልሶች እንድትሰጡኝ በማለት ቃለ መጠይቁን በመመለስ ለምታደርጉልኝ ትብብር በመጀመሪያ አመሰግናለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ**

የትምህርት ቤት ስም ……………………………………………

ፈረቃ ………………………..

ምልከታ የተደረገበት ቀን …………………………

ምልከታ የተደረገበት ሰዓት …………………………

ክፍል ና ድልድል ………………………………

**የመምህሩ አጠቃላይ መረጃ**

የትምህርት ደረጃ ……………………………..

የስራ ልምድ …………………… ጾታ …………

**ክፍል አንድ**

መምህሩ ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ነበራቸው ………………አልነበራቸውም …………….

የዕለቱ የትምህርት ርዕስ ……………………………………………………………..

የዕለቱ የትምህርት ዓላማዎች ……………………………………………………..

መምህሩ የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በቃል ………………………………………..

በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ……………………………………………………………

**ክፍል ሁለት**

በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ መለማመጃ ላይ መምህራን የሚሰጡት ግብረ መልስን በተመለከተ የተዘጋጀ የምልከታ ቅጽ፡

5- በጣም ዝቅተኛ 4- ዝቅተኛ 3- መካከለኛ 2- ከፍተኛ 1- በጣም ከፍተኛ

| ተ.ቁ | የቀረቡት ጥያቄዎች | ምርጫዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1. | የተማሪዎች የመለማመጃ ጽሑፍን በተመለከተ መምህራን በሚሰጡት ግብረመልስ መደረግ ያለባቸው ተግባራት፡ | | | | | |
| 1.1. | መምህሩ በተማሪዎች የጽሑፍ መለማመጃ ላይ የሚጠቀሙበትን ዘዴ ይጠቁማሉ ? | | | | | |
| 1.2. | መምህሩ ለተማሪው የሚሰጡት ግብረመልስ ለቀጣይ ጹሁፋችው እገዛ ያደርጋል? | | | | | |
| 1.3. | ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሑፎች ላይ የሚታዩትን የሰዋሰው ስህተቶችን እንዲያስተካክሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ? | | | | | |
| 1.4. | ለተማሪዎች የሚሰጠው ግብረመልስ የራሳቸውን ተነሳሽነትን ይፈጥራል? | | | | | |
| 1.5. | ተማሪዎች በሚጽፏቸው የጽሑፍ መለማመጃ ላይ የቃላት አጠቃቀማቸውና የዓረፍተነገር አወቃቀራቸውን በተመለከተ የትኛውን የግብረ መልስ አይነት እንደተጠቀሙ ይገልፃሉ? | | | | | |
| 1.6. | ተማሪዎች የራሳቸውን የአጻጻፍ ስልት እንዲከተሉ መምህሩ ያበረታታሉ? | | | | | |
| 2. | የተማሪዎችን የጽሑፍ መለማመጃ በመተለከተ ድርሰትን የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት፡ | | | | | |
| 2.1. | ተማሪዎች የጻፉትን ድርሰት እርስ በእርስ እርማት እንዲሰጣጡ ያደርጋሉ ? | | | | | |
| 2.2. | የመምህሩ ግብረመልስ በተማሪዎች ስሜት ላይ አፅኖኦት ያደርጋል ? | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.3. | ለተማሪዎቻቸው እርማት ሲሰጡ በጽሑፍ መለማመጃቸው ላይሊረዱ የሚችሉትን ምልክቶችን በመጠቀም ግብረመልስ ይሰጣሉ ? | | | | | |
| 2.4. | የተማሪዎችን ስህተት በመለየት የትኛው የግብረ መልስ አይነት አሰጣጥ ለመጻፍ ክሂላቸው መሻሻልና ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ስልት ይገልጻሉ? | | | | | |
| 2.5. | በተማሪዎች ድርሰት አጻጻፍ ላይ የሀሳብ ፍሰትና አደረጃጀት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ? | | | | | |






NO MORE



















NO MORE







ገለጻ የሆኑ ... ከማድረግ አኀይመንት

የቤት መሠረት አወጣጥ

ቤት ሲሠራ ዋናውና ከርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሠረት ነው። መሠረት ያልጠነከረ ቤት ቆይ-
ቶ አይቆይም። መሠረቱ ቤቱን በትክክል ካልያዘ የመሠረት ሰው አይከኝ አውኩንኩሉ እና
ሄን ሬመጣ አይሰጥም" እንዲሚገነው ቤት የሚሠራ ሰው ሁሉ ከመሠረቱ ማንሳት ቀጥ
ሚያ ሰማይ መንቀሳቀስ አለበት። የቤት መሠረት ከሚሩፍበት የሚገባው ቦታ ወይፍ ንጣፍ
ድንጋይ ሳለለማሪ ድሎስ ይቆፈራል

=> ቤት ሲሠራ ዋናውና ከርቱ ጠንቃቄ የሚያስፈልገው መሠረት ነው ስለዚህ አንድ ቤት ከመስራት
ከመጀመሩ በፊት ሐሳብ መጠቀኛ መሠረቱን የጠበቀ መሆን አለበት። ቤት ከመስራት በመጀ-
መሪያ ቦታ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ቤት የሚሰራበት ቦታ ከተገኘ በኋላ ቤቱን ከመስራት የሚያ-
ስፈልጉትን ቁሳቁሶች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ከምሳሌ ግንባታ ቤት ከመስራት አስፈላጊ
ቁሳቁሶች የሆኑት ከመቆፈር የሚያስፈልጉት፡ ዶማ፡ ማረሻ እና አካፋ ሲሆን ከመቁረጥ ደግሞ
መጋዝ እና መጥረቢያ ሲሆን ከመመተር የሚያስፈልጉትን ውሃ ልክ፡ መዶሻ፡ እና ሜትር
ከመለካት መጫኛ (ፋስ) እና የመሳሰሉት ናቸው። ቤቱን ከመገንባት የሚያስፈልጉት (ቤት ለማንኛውም እን
ንዲሚሰራ ወይም አስፈላጊ ነገሮች) የሆኑት ድንጋይ፡ ውሃ፡ ሎሚ፡ ሲሚንቶና አሸዋ፡ ብረት፡ ብሎኬ
ት፡ ቆርቆሮ፡ ቀለም፡ መስኮቶች፡ በሮች፡ ሴራሚክ እና የመሳሰሉት ናቸው።


ከመገንባት ከሚያስፈልጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ እና አስፈላጊው ድንጋይ ነው። የቤት ግንባታው
ስጥ የድንጋይ ጥቅም አንድ ቤት መሰረት ጥሩ አረጅ አመታት እንዲቆይ ያደርጋል፡ [illegible]
ሪት እንዲይዝ፡ ቤቱ ውሃ እንዳያስገባ እና የመሳሰሉት ናቸው ጥቅሞቹ ናቸው።


ውሃ፡ ሲሚንቶ እና አሸዋ እነዚህ ቁሳቁሶች ደግሞ አንድ አይነት ጥቅም ለቤት ግንባታ ይሰጣሉ።
ጥቅማቸውም፡ አንድ ላይ በመቀላቀል መከላ እና ግርግዳ ከመስራት ይጠቅማል። ውሃ፡ ለተለያየ
ስራ ውስጥ አንዱ ሆኖ ለሰው ልጅ በዙ ጥቅም አለው። እንዲሁም ለሕይወት ውስጥ አንድ አካ
ል ነው። ለግንባታ ይጠቅማል ስለዚህ ደግሞ አሸዋና ሲሚንቶ ከማጣበቅ እና ከማጠጣት
ይጠቅማል። ሲሚንቶና አሸዋ ደግሞ መከላ እና ግርግዳ (ቦካቴት) ከማያያዝ ይጠቅማል።


ለቤት ግንባታ ከሚያስፈልጉት ነገሮች መካከል ሌላኛው መስታወት ነው። መስታወትም ከ-
አሸዋ የሚሰራ ሆኖ ለግንባታ ጥቅሙ መስኮት እና ... ለመስራት ይጠቅማል ነው።


ሎሚ፡ ቆርቆሮ፡ ብሎኬት እና ብረት እንዲሁም ዝርዝ ሆነው ጥቅማቸው ግን የተለያየ ነው። እነ
ዚ ብረቶችም የብረት አይነቶች ነው። ብረት ደግሞ የተፈጥሮ ሀብት ነው። ብረት የተፈጥሮ ሀብት
ነው ስንል ከሚፈጥሩ ውጭ የሚገኝ ነው ማለት ነው። ከብረት ቆርቆሮ ይሰራል። ቆርቆሮም
ለቤት ግንባታ ጣሪያ እንዲሰራ ይጠቅማል። ሌላኛው ከብረት የሚሰራ ደግሞ ሚስማር ነው።
ለቤት ግንባታ ሎሚ የሚጠቅመው ቤት መስራት እንዲቆረጥ እና እንዲጠነክር ይ-
ጠቅማል። ብሎኬትም ከብረት ይሰራል። ብሎኬትም ለቤት ግንባታ ብረቶችን ከመገጣጠ
ም ይጠቅማል።


— የሎሚ ስ ለ ግንባታ ጥሩ ትኩረት...
— ዋ ልጆ መ ያ ርዓ ቁሳቁሶች
— [illegible]
እስኪር... [illegible]



ተገገዷል
መልካም ሣኪዩል!!!




















# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸዉ የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰጧቸዉ ግብረ መልሶች ትንተና (በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በደብረ ጽጌ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት የራሴ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸው ዋቢ ፅሑፎች በሙሉ ምንጫቸውን የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡ -------------------------------------

ፊርማ፡ -----------------------------------

ቀን፡ ---------------------------------------

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዝም እና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ-ጥበብና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር